## 1. በቁልፍ የትኩረት መስክ

የአቅም ግንባታ ኘሮግራሞችን ቀጣይነትና ዘላቂነት ባለው ሁኔታ ለመተግበር እንዲያስችል የተፈጠረ ቅንጅታዊ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም፣

### 1.1 የታቀዱ ዝርዝር ቁልፍ ተግባራት /ውጤቶች/

- የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም፣ የመልካም አስተዳደር መርሆዎችና የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ኘሮግራሞች በመንግሥት መ/ቤቶች በተለወጠና በተሟላ መልኩ እንዲፈጸሙ ግብዓት በመስጠት የማስፈጸም አቅምን መገንባት፣
- ጥናታቸው ተጠናቆ በአዲስ የሥራ ሂደት በመግባት ዓመታዊና 2ኛ መንፈቀ ዓመት ውጤት ተኮር ዕቅድ አዘጋጅተው ምዘና የጀመሩ 63 የዞንና የወረዳ መ/ቤቶች
- ጥናታቸው በመጠናቀቅ ያሉና ዓመታዊ የተቋምና የ6 ወራት የቡድንና የሠራተኛ ውጤት ተኮር ዕቅድ ከዝግጅት እስከ ምዘና የገቡ 72 የዞንና የወረዳ ሴ/መ/ቤቶች
- በዕቅድ ዝግጅትና ትግበራ ያለውን የአቅም ክፍተት ለማሟላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና የተቀበሉ 291 የዞንና የወረዳ አመራሮችና የሥራ ሂደት አስተባባሪዎች
- በመልካም አስተዳደር ፖኬጅ አዋጆችና መመሪያዎች አፈጻጸም መልካም ተሞክሮዎችን ለማስፋት ለ3213 የገጠር ወረዳ ቀበሌያት አመራሮች አቅም ለመገንባት የተካሄደ የውይይት መድረክ፣
- ለ3 የዞንና ለ21 የወረዳ ኢንስፔክሽን አባላት አቅም ለመፍጠርና ለጋራ ግንዛቤ የተመቻቸ የውይይት መድረክ
- የመፈጸም ክፍተትን ለመሸፈን በተዘጋጀ የጋራ ውይይት መድረክ የተሳተፉ 1071 የቀበሌ የኢንስፔክሽን ቡድን አባላት።
- የ119 የገጠር ቀበሌያት በአገልግሎት አሰጣጥና የዕቅድ ዝግጅት ስኬት የአቅም ግንባታ ሥልጠና የተሰጣቸው 119 የቀበሌ ሥራ አስኪያጆች
- ከ119 የገጠር ቀበሌያት ምርጥ ተሞክሮን ለማስፋት በሞዴልነት የተመረጡ 50 የገጠር መንደሮችና 35 ቀበሌያት
- ከ238 ታዋቂ ግለሰቦችና የቀበሌ ሊ/መናብርት ጋር በመልካም አስተዳደር መርሆዎች አሳምኖ የማሰራት ባህልን ለማዳበር የተዘጋጀ የግንዛቤ መድረክ
- የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ኘሮግራምን በዞንና በወረዳ ባሉት የፍትህ ተቋማት ለማሳካት የአቅም ግንባታ ሥልጠና የተሰጣቸው 132 አመራሮችና ባለሙያዎች
- ለ890 የመንግሥት ሠራተኞችና ለተለያዩ የኀ/ሰብ ክፍሎች ስለ ፍትህ ሥርዓት ያላቸውን ግንዛቤ ለማስፋት የተፈጠረ የውይይት መድረክ
- 7 ሺህ ከዞን እስከ ገጠር ቀበሌያት ተግባራዊ የተደረገ የኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ መርህ ት/ት
- ተዳራሽነቱ በተረጋገጠ ሁኔታ አገልግሎት መስጠት የቻሉ የዞንና የወረዳ የፍትህ ተቋማት
- የዜጐችን መብትና ግዴታ ለማስከበርና የወንጀልን አስከፊነት ለማስረዳት ለ1132 የኀ/ሰብ ክፍሎች የተሰጠ የንቃተ ሕግ ትምህርት

- የዜጎችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ለማስከበር፣ የሕግ ታራሚዎች ከወንጀል ድርጊታቸው ፀድተውና መልካም ሥነ-ምግባር ተላብሰው ወደ ኅ/ሰቡ እንዲቀላቀሉ የተሰጠ የሕግ፣ የቀለም፣ የሙያና የግብረገብ ትምህርት
- በዞንና በወረዳ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ የቴክኒክና የአስተባባሪ ኮሚቴዎች በድጋፋዊ ክትትል ውይይትና ግምገማ የተያዘ መረጃ
- የማስፈጸም ክፍተትን ለመለየት በተካሄደ የዳሰሳ ጥናት የተሰበሰበ መረጃና የተዘጋጀ ማኑዋል
- በዞንና በወረዳ ባሉት የመንግሥት መ/ቤቶች የክፍተት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ የማስፈጸም ውስንነት ለመቅረፍ ግብዓት በመስጠት አዲሱን የአሠራር ሂደት ትግበራ ማሳካት
  - ❖ በዞኑ ICT እንዲስፋፋ በማድግ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍንና ቀልጣፋና ተደራሽ የሆነ አገልግሎት አሰጣጥ እንዲፈጠር ተቋማትንና ኅ/ሰቡን የዘመናዊ መረጃ ልውውጥ ተጠቃሚ ማድረግ
- 2 መለስተኛ ዝርጋታና 2 ሙከረና ክለሳ የተደረገላቸው የዘመናዊ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ተጠቃሚ ሴ/መ/ቤቶች
- የዳበረ የኮምፒዩተር አጠቃቀም ክህሎት ያላቸው 100 የመንግሥት ሠራተኞች
- ለ52 ቪዲዮ ኮንፍረንሲንግ አገልግሎት እንዲውል የተሠራ ኮንፊግሬሽንና ሙከራ አገልግሎት
- ለ48 ቀላል ብልሽት የተሰጠ ጥገና
- ስፔስፊኬሽን በማዘጋጀት በየሥራ ሂደቱና በግዢ ሥራ ሂደት የተፈጸሙ ግዢዎች
  - ❖ 132 የዞን፣ የወረዳና የዱራሜ ከተማ ሴ/መ/ቤቶች ባለሙያዎችና ሠራተኞች በፍላጐት ላይ የተመሠረተ ትምህርት ሥልጠና በመስጠት ጥራትና ብቃት ያለውን የሰው ሀብት ማፍራት
- በ61 መ/ቤቶች የተደረገ ጥናትና የተሰጠ ምክር አገልግሎት
- በግልጸኝነትና በፍትሃዊነት የተመለመሉ ሠራተኞች
- ለ200 ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የተሰጠ ሥልጠና
- የተገኘ የውጭ ሀገርና የሀገር ውስጥ ትምህርትና ሥልጠና

❖ የሜሪትን ሥርዓት የተከተለ፣ ዘመናዊ ቀልጣፋና ለለውጥ ዝግጁ የሆነ የሰው ሀብት አመራር ሥርዓት በመዘርጋት በመ/ቤቱ ሥር የሚካሄደውን ልማታዊ ሥራና የመልካም አስተዳደር እንቅስቃሴ መደገፍ

- ➢ በአዲሱ የሥራ ሂደት የገቡትን የሴክተሩን /6 የሥራ ሂደቶች/ አቅም በማጐልበት ከተሟላ ዕቅድ አፈጻጸም ጋር የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ተገልጋዮችን 100% ያረኩ እንዲሆኑ ማስቻል፣
  - በዕቅዶቻቸው መሠረት የሰው ሀብት ክፍተት ለለባቸው 2 የሥራ ሂደቶች በቅጥር ፣ በዝውውር፣ በደረጃ ዕድገት የተሟሉ ሠራተኞች
  - ወቅታዊ፣ ትክክለኛ፣ የተሟላና በማንኛውም ጊዜና ቦታ ተአማኒነትና ተደራሽነት ያለውን መረጃ ቀልጣፋና ፈጣን በሆነ መንገድ በመሰብሰብ፣ በማደራጀትና በማሠራጨት የዞኑን ልማትና መልካም አስተዳደር እውን ማድረግ

- በመረጃ አያያዝና አደረጃጀት ትኩረት ተሰጥቷቸው የውስጥ አሠራራቸውን እንዲያሻሽሉ የተደረጉ 9 የዞንና የወረዳ አቅም ግንባታ ጽ/ቤቶች
- ከዞንና ወረዳ አቅም ግንባታ ጽ/ቤቶች ተሰብስበው የተተነተኑ፣የጠሩና ወደ ኮምፒዩተር የገቡ ልዩ ልዩ መረጃዎች
- በዞን፣በዱራሜ ከተማና በ7ቱ የገጠር ወረዳዎች ውስጥ በሚገኙ 9 የአቅም ግንባታ ሴክተር መ/ቤቶች የተጠናከረና የተቀናጀ የልማት ዕቅድ ዝግጅት፣ክትትል፣ ግምገማና ግብረ መልስ ሥርዓት በመዘርጋት የማስፈጸም አቅምን ማጐልበት
- በተዘጋጀው ማኑዋል ላይ የተወሰደ ሥልጠና
- የ2001 በጀት ዓመት /የ2ኛው መንፈቀ ዓመት / ተከልሶ የተዘጋጀ ተቋማዊ ዕቅድ
- የተካሄደ የ5 ዓመት/1998-2002/ ስትራቴጂክ ዕቅድ ግምገማና የቀሪ ዓመታት /2001-2002/ ዕቅድ ክለሳ ሪፖርት
- በሴክተር ደረጃ የተዘጋጀ መወኘ /መኢኘ
- በበጀት ኮድና በየሥራ ሂደቱ /የወጪ ማዕከሉ/ በዝርዝር የተዘጋጀ ዓመታዊ ዕቅድና በጀት
- በሴክተር ደረጃ የተዘጋጀ የድርጊት መረሃ ግብር
- የተቀናጀ /የመንግሥት፣የመያድና የኅ/ሰብ ድርሻ በግልጽ  የሚያመለክት አሳታፊ የልማት ዕቅድና ወጥ አሠራር
- የበጀት ዓመት ከመድረሱ በፊት አንድ ወር አስቀድሞ የተገለጸ የዕቅድና በጀት ዝግጅት

3.2. የተከናወኑ ዝርዝር ቁልፍ ተግባራት ፣

I. የመሠረታዊ ሥራ ሂደት ለውጥ የሙሉ ትግበራ በተመለከተ፣

በእቅዱ መሠረት ወደ ሙሉ ትግበራ በገቡ በ63 የዞንና የወረዳ መ/ቤቶች መከናወን የሚገባቸው ተግባራት በተመለከተ ፣

1.1. መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጡ ወደ ሙሉ ትግበራ ከመገባቱ በፊት በለውጡ ምንነት ፣አስፈላጊነትና በአፈፃፀም ደረጃዎቹ ላይ የአመራሩን ግንዛቤ ለማዘጋጀት አንድ የከተማ አስተዳደርን ጨምሮ ለ7ቱ የገጠር ወረዳ አቅም ግንባታ ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ምክትሎች የመጀመሪያ ዙር የግንዛቤ መድረክ በክልሉ የሥልጠና መነሻ ለአንድ ቀን የተፈጠረ ሲሆን ቀጥሎም ጥናቱ በተጠናቀቀባቸውና እየተጠናቀቀ በሚገኝባቸው በዞንና በወረዳ መ/ቤቶች ከ268 ለሚበልጡ አመራሮችና የሥራ ኃላፊዎች ስለለውጡ ጠቀሜታና ስለለውጥ አመራር ስትራቴጂ የሁለት ቀን ሥልጠና ተሰጥቶ በቂ ግንዛቤ እንዲጨበጥ ተደርጓል፡፡ ከዚህ ጋር እያንዳንዱ መ/ቤት ስለሙሉ ትግበራው መርሃ ግብር እንዲዘጋጅ ተደርጐ በዋናነት በደንብ ቁጥር 72/2001 አተገባበር ላይ በጋራ ውይይት ግንዛቤ ከተፈጠረ በኋላ በመርሃ ግብሩ መሠረት ኮሚቴ የማዋቀር፣ማስታወቂያ

የማውጣትና የውድድር መስፈርቶችን ለይቶ የማዘጋጀት ሥራ እንዲሠራ ክትትል ተደርጓል፡

1.2. መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጡ እንደዞናችን ተጨባጭ ሁኔታ በተወሰነ መጠን የግብርናው ሴክተር ሥልጠና ከመዘግየቱ በስተቀር በሌሎች ሴክተሮች የአጀማመር ሥልጠና በተዘጋጁ ማኑዋሎች ላይ በወቅቱ በመሰጠቱ ከጥር አጋማሽ ጀምሮ በአብዛኞቹ መ/ቤቶች የሚገኙ ሥራ ሂደቶች ወደ ሙሉ ትግበራ ገብተዋል፡፡

1.3. ከአንድ ማዕከል የሚጠበቀው ቀልጣፋ አገልግሎት በተሟላ መልኩ በሚፈለገው አይነት እንዲሰጥ የሥራ ሂደት አስተባባሪዎችና ፈፃሚ ባለሙያዎች በአንድ ላይ ሆነው ምልልስ ሣያስፈልግ መሥራት እንደሚጠበቅባቸው የታወቀ ሲሆን በዚሁ መሠረት በዞንና በወረዳ ወደ ሙሉ ትግበራ በገቡ በ63 መ/ቤቶች ከሚገኙ የሥራ ሂደቶች መካከል ከ75% በላይ በሚሆኑ የሥራ ሂደቶች ፈፃሚ ባለሙያና አስተባባሪ በአንድ ላይ በመሆን የተቀናጀ አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል፡፡

1.4. በዞኑ በሚገኙ መ/ቤቶች መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጡ ወደ ሙሉ ትግበራ ሲገባ በየመ/ቤቱ ያሉ የሥራ ሂደት አስተባባሪዎችና ፈፃሚዎች የተጠናከረ ባይሆንም የግብዓት ማሰባሰቢያ ቅፃ ቅፆችንና ቼክ ሊስቶችን አዘጋጅተው ትግበራውን የጀመሩ ሲሆን ከእነዚህ መካከል የፋይናንስ ኢኮኖሚ፣ የሥራ ከተማ ልማት እና የንግድ ኢንዱስትሪ ሴክተሮች አንፃራዊ ጥረት በማድረግ የተለዩ ናቸው፡፡

1.5. በየደረጃው በድልድሉ እንዲሣተፉ የተደረጉ ፈፃሚ ባለሙያዎችና አስተባባሪዎች ለሙሉ ትግበራ ብቁ በሚያደርጋቸው በትግበራ ማኑዋልና በቲም ቻርተር ላይ ሥልጠና እንዲወስዱ ከክልል ጀምሮ የተቀመጠው አቅጣጫ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ የተደረገ ቢሆንም 148 ሠራተኞች የዘገየ ምደባ የተሰጣቸው በመሆኑ ክልላዊ ሥልጠና ሣይሣተፉ ወደ ሙሉ ትግበራ እንዲገቡ የተደረጉ መሆኑን የድጋፋዊ ክትትል መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

1.6. ከለውጥ አመራር ሥራዎች አንዱ የለውጥ ተቃውሞን በአግባቡ መያዝና መምራት ሲሆን ስለ ለውጡ በበቂ ሁኔታ ካለመረዳት፣ ለውጡ የሚያስከትለውን ሁኔታ ከመስጋትና ከለውጡ ጋር ለመራመድ ከቅም ማነስ በሚመነጩና በሌሎችም ምክንያቶች የሚነሱ የተቃውሞ አዝማሚያዎችን ለመስበር በየሴክተሩ በቂ የሠራተኞች የውይይት፣ የምክክርና የግንዛቤ መድረኮች በስፋት እንዲፈጠሩ

ተደርጐ የተቃውሞ አያያዝና የአመራር ስልቶቹ በተሻለ መልኩ ተጠናክረው ቀጥለዋል፡፡ ከዚህ የተነሣ በአሁኑ ወቅት ሠራተኞች ለውጡን በእምነት በመቀበል በሚያበረታታ መነሣሣት ውስጥ ያሉበት ሁኔታ ስለሚታይ ጥናቱ እየተጠናቀቀ ለሚገኝባቸው መ/ቤቶችም በአብነት ወደ መጠቀስ ደረጃ እየተደረሰ ይገኛል፡፡

1.7. መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ተግባራዊ ለማድረግ የሠራተኞችን ድልድል ለማስፈፀም በወጣ ደንብ ቁጥር 72/2001 ክፍል ሁለት በአንቀጽ 10 የሥራ ሂደት አስተባባሪዎች አመዳደብ በሹመትና በምደባ እንደሚሆን ከመደረጉ ጋር ተያይዞ ጥናቱ ተጠናቆ ወደ ሙሉ ትግበራ በተገባባቸው በዞንና በወረዳ መ/ቤቶች የሥራ ሂደት አስተባባሪዎች ምደባ በሹመትና በሜሪት በወቅቱ የተጠናቀቀ ስለሆነ በምደባው ዙሪያ ያጋጠሙ ችግሮች የሌሉ መሆኑን በድጋፋዊ ክትትል ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

1.8. በየመ/ቤቱ የሚካሄደው የሠራተኞች ድልድል ግልጽ፣ ተጨባጭና ፍትሃዊ እንዲሆን በድልድል ደንብ ላይ የተቀመጡ የድልድል መስፈርቶች ለተደልዳይ ሠራተኞች በየመ/ቤቱ መርሃ ግብር መሠረት በውይይት ግንዛቤ እንዲፈጠርባቸው የተደረገ ከመሆኑም በላይ መስፈርቶቹ በየመ/ቤቱ ግልጽ በሆነ ሥፍራ ተለጥፈው ባለሙብቱ በማንኛውም ጊዜ ክትትል እንዲያደርግ የተመቻቸ ሁኔታ የተፈጠረ ሲሆን በደንብ ቁጥር 72/2001 ክፍል ሶስት በአንቀጽ 12 የተመለከቱትን መስፈርቶች መሠረት አድርጐ የ1542 ሠራተኞች ምደባ በወቅቱ ተከናውኗል፡፡

1.9. ምንም እንኳን ምደባዎች ግልጽና ፍትሃዊ እንዲሆኑ በቂ ጥረት የተደረገ ቢሆንም አልፎ አልፎ ቅሬታዎች መነሣታቸው አልቀረም፡፡ ቅሬታዎቹ ከተነሱባቸው አቅጣጫዎች አንዱ የሥነ ምግባር፣ የአገልግሎት አሰጣጥና የለውጥ ተነሣሽነት መስፈርቶች ላይ መሆኑን የክትትል መረጃዎች የሚያመለክቱ ሲሆን በዚህ በኩል ከፋይናንስ እና ከንግድና ኢንዱስትሪ ሴክተሮች ለተነሱ ቅሬታዎች በወቅቱ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ በሌላ በኩል ከመመሪዎች አተረጓጐም የግንዛቤ ክፍተት ጋር ተያይዘው ለቀረቡ ለ39 ቅሬታዎች በደንብ ቁጥር 72/2001 መሠረት የማስተካከያ ምላሽ ለመስጠት ተችሏል፡፡

1.10. የሠራተኞችን የምደባ ተገቢነት ከማረጋገጥ አንፃር በዞንና በወረዳ መ/ቤቶች ባሉ የሥራ ሂደቶች የተመደቡ ሠራተኞችን ተገቢነት ከሙያ መስመር ፣ከት/ት ዝግጅትና ከሥራ ልምድ አግባብነት ለአዲሱ የሥራ መደብ የተጣጣመ መሆኑን

በየደረጃው በሚገኙ በአቅም ግንባታ ጽ/ቤቶች በኩል ክትትል ለማድረግና ለመለየት የተቻለ ከመሆኑም ባሻገር ደንብ ቁጥር 72/2001 ተከትለው የተላለፉ የት/ትና የሥራ ልምድ ማሻሻያዎችም ተካተው ተግባራዊ ተደርገዋል።

1.11. በውድድሩ የታቀፉና የቀሩ ሠራተኞችን መረጃ ለመከታተል በተደረገው ሂደት በየመ/ቤቱ ባሉ የሥራ ሂደቶች ተወዳድረው ሣያልፉ በመቅረት ካለፉት ጋር በስህተት ተቀላቅለው እንዲሠሩ የተደረጉ ሠራተኞች አለመኖራቸው የተረጋገጠ ሲሆን በየመ/ቤቱ ተወዳድረው ምደባ ያላገኙ ሠራተኞች መረጃ በወቅቱ ተጠናቅሮ ለአቅም ግንባታ ጽ/ቤቶች እንዲቀርብ በመደረጉ ከመ/ቤቶች ጋር ተናቦ ለመሥራት ተችሏል።

1.12. የድልድሉን ሂደት በዋናነት የሚመራው ኮሚቴ በየመ/ቤቱ በደንብ ቁጥር 72/2001 ክፍል ሁለት በአንቀጽ 6 በሚጠቅሰው አግባብ እንዲቋቋም ተደርጐ ተግባርና ኃላፊነቱ ከተገለጸ በኂላ በየደረጃው የተጣለባቸውን አደራ ከመወጣት አንፃር ቃለ-መሃላ በመፈጸም ወደ አሠራር የተገባበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ተደርጓል።

1.13. በድልድሉ ለታቀፉ ለ1542 ሠራተኞች በድልድል ደንቡ በተቀመጠው የአፈፃፀም መሠረት የተመደቡበትን የሥራ ሂደት፣ የሥራ መደብ መጠሪያና የያዙት ደመወዝ መጠን ብቻ የሚገልጽ ደብዳቤ እንዲሰጥ የማድረጉ ሥራ ያለምንም ክፍተት ተግባራዊ ሆኗል።

1.14. እስከአሁን በተገኘው መረጃ መሠረት በዞኑ በየሴክተሩ በተፈቀዱ የሥራ ሂደቶች ላይ የተመለከቱትን የት/ት ዝግጅት ፣ የሙያ መስመርና የሥራ ልምድ መስፈርቶችን በተከተለ አግባብ

1/ የአቅም ግንባታ ሴክተር 75.2 %

2/ የት/ት ሴክተር 84.67%

3/ የግ/ገ/ል/ ሴክተር 88.3%

4/ የፋይ/ኢኮ/ል/ሴክተር 84.5%

5/ የንግድ ኢንዱስትሪ ሴክተር 73%

6/ የሥራና ከተማ ልማት ሴክተር 60.9%

7/ ፖሊስ ሴክተር 34%

8/ ማረሚያ ሴክተር 53% ከዞን እስከ ወረዳ በሰው ኃይል የተያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፣

1.15. በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ በሠራተኞች ድልድል ወቅት በተለያየ ምክንያት መስፈርቱን ሣያሟሉ የቀሩ ሠራተኞች ሁሉም በየመ/ቤቱ ከ50% በላይ ውጤት ያመጡ ሲሆን ያልተመደቡበትም በውጤት ማነስ ሣበሆን በአፈፃፀም ክትትል ወቅት ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

1.16. ከዞን እስከ ወረዳ ወደ ሙሉ ትግበራ በገቡ መ/ቤቶች ለሥራ ሂደቶች ምቹ የሥራ ቦታዎችንና ቢሮዎችን ከማዘጋጀት አንፃር፣ በአቅም ግንባታ ሴክተር የአንጋጫ ወረዳ አቅም ግንባታ ጽ/ቤት የኃላፊ ቢሮን ለለውጥ ኘሮግራሞች የሥራ ሂደት በመፍቀድ ፣በግብርናና ገጠር ልማት ሴክተር የቃጫ ቢሮ ወረዳ ም/ኃላፊ ቢሮ ለኤክስቴንሽን ሥራ ሂደት መለቀቁ፣ በጠምባሮ ግ/ገ/ል/ ጽ/ቤት ለሥራ ሂደቶች በሙሉ ጠባብ ቢሮዎችን አፍርሶ በማገናኘት ሰፊ ክፍሎች እንዲፈጠሩ መደረጉና ተመሣሣይ ተግባር በሃደሮ ጡንጦና በቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ ግ/ገ/ል/ጽ/ቤቶች መከናወኑ፣ በዶዮገና ወረዳ ግ/ገ/ል/ጽ/ቤት ለኤክስቴንሽን ሥራ ሂደት መለስተኛ አዳራሽ መፈቀዱ የሚጠቀሱ ተግባራት ሲሆኑ በሥራና ከተማ ልማት ሴክተር የሙዱላ እና የዳምቦያ ማዘጋጃ ቤቶች የኃላፊ ቢሮዎችን ለገቢ ሂሣብና በጀት የሥራ ሂደቶች መሰጠቱ፣ የሺንሺቾና የዶዮገና ማዘጋጃ ቤቶች ክፍሎችን አፍርሶ ሰፋፊ ቦታዎች እንዲዘጋጁ መደረጉ፣ በፋ/ኢ/ል/ዘርፍ የዞኑ መምሪያ በቂ የሥራ ክፍሎች የተዘጋጁለት ከመሆን ጋር የመንግስት ፋይናንስ የሥራ ሂደት የተሻለ ቢሮ ተዘጋጅቶለት በአይቤክስ (IBEX) ከወረዳ እስከ ዞንና ክልል ተገናኝቶ የመረጃ ልውውጥ እንዲደረግ ሁኔታዎች መመቻቸታቸውና በንግድ ፣በት/ትና በፓሊስ መምሪያዎች ተመሣሣይ እንቅስቃሴዎች እንዲቀጥሉ በድጋፋዊ ክትትል ወቅት አቅጣጫ እንዲቀመጥ መደረጉ የሚጠቀሱ ተግባሮች ናቸው፡፡

1.17. ለሥራ ሂደቶች የሚያስፈልጉ ቁሣቁሦችንና መሣሪያዎችን በማቅረብ ረገድ የዱራሜ ከተማ ማኀበራዊ አገ/ት አቅ/ግንባታ ለኢኮቴ የሥራ ሂደት ኮምፒዩተር ከነኘሪንተሩ ገዝቶ ማቅረቡ፣ በግብርናና ገጠር ልማት የሃደሮ ጡንጦ ዙሪያ ወረዳ አራት ጠረጴዛና 24 ወንበር አሠርቶ አገልግሎት ላይ ያዋለ መሆኑ ፣ የአንጋጫ ወረዳ ግ/ገ/ል/ጽ/ቤት ለኤክስቴንሽን ሥራ ሂደት የሚውል ሞተር ብስክሌት ለመግዛት ጨረታ በመጠባበቅ ላይ መገኘቱ፣ በሥራና ከተማ ልማት የአንጋጫ፣ የሺንሺቾና ፣የሙዱላ ማዘጋጃ ቤቶች እስከኮምፒዩተር ግዥ የደረሱበት ሁኔታ መኖር፣ የሃደሮ ጡንጦና የዳምቦያ ማዘጋጃ ቤቶች ወንበርና ጠረጴዛ ገዝተው

ለሥራ ሂደቶች ማቅረብ መቻላቸው የተወሰኑ አብነቶች መሆናቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

1.18. የተጀመረውን መሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጥ በበጀት ከመደገፍ አኳያ የአንጋጫ ወረዳ አቅም ግንባታ ጽ/ቤት ከራሱ በጀት በወረዳው የተደረጉትን የማስፈጸም አቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን በመለስተኛ ሎጀስቲክ ለመደገፍ መቻሉ፣ የቀዲዳ ጋሜላና የጠምባሮ ወረዳ አቅም ግንባታ ጽ/ቤቶች በካቢኔ ውሣኔ በመታገዝ ተመሣሣይ የሥልጠና ሁኔታ ማሣካት መቻላቸው እና የዞኑ አቅም ግንባታ መምሪያ ከራሱ በጀት ሥልጠናዎችን ለማመቻቸት የተደረጉ ጥረቶች ሊበረታቱ የሚገቡ ጅምር ድጋፎች ሲሆኑ የዞኑ ስትሪንግ ኮሚቴ የዞኑን መሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጥ ከገመገመ በኋላ በሙሉ ትግበራ ውስጥ ለሚገኙ ሴክተሮች በካቢኔ ተስኖ የበጀት ድጋፍ እንዲሰጥ መደረጉ በዋናነት የሚጠቀሱ ተግባሮች ናቸው፡፡

1.19. ቲም ስፒሪት ከማሣደግ አንፃር በየሥራ ሂደቱ ጠባቂነት ሣይኖር፣ እለታዊ፣ሣምንታዊና ወርሃዊ ሥራዎችን በአገልጋይነት ስሜት ከጅምር እስከ ፍፃሜ ተግቶና ተተካክቶ የመሥራት ልምድ እየዳበረ የመጣ ሲሆን ለአብነት የዶዮገና የቃጫ ቢራ ፋይናንስ፣በንግድ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የዞኑ የሆቴሎች፣ ፓርኮችና ቱሪዝም የሥራ ሂደት በዞናዊ ንጽጽር የሚጠቀሱ ይሆናሉ፡፡

1.20. እያንዳንዱ መ/ቤት ደጋፊ የሥራ ሂደቶችን ከራሱ ተጨባጭ እያጣጣመ ለሥራ ሂደቱ የተመደቡትን ኦፊሰሮች በየደረጃው የማብቃት ሥራ እየሠራ ወደ ተግባር እንዲገባ ተደርጓል፡፡

1.21. እስካሁን በፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማትና በአቅም ግንባታ ሴክተሮች የተጠኑ ደጋፊ የሥራ ሂደቶች በየመ/ቤቱ ተግባራዊ ቢደረጉም እነዚህ ደጋፊ የሥራ ሂደቶች በዋናነት በተጠኑ ሴክተሮች በኩል ክትትል እየተደረገ ድጋፍ ሊሰጥ እንደሚገባ ይታወቃል፡፡ በዚህ ረገድ የሥራ ሂደቶቹ ተግባር የተሣካ እንዲሆን በአጥኚውና በተግባሪው መ/ቤቶች መካከል ቅርብ የአሠራር ግንኙነት እየተፈጠረ የሥራ ሂደቶቹ እንዲጠናከሩ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

1.22. ቀደም ሲል በመተግበር ላይ የነበሩ የምልመላ መረጣና የሰው ሃብት ሥራ አመራር ደንቦችና መመሪያዎች በአሁኑ ወቅት በሚወጡ በአዳዲስ ደንቦችና መመሪያዎች እየተተኩ የሚገኙ ሲሆን ከዚህ ጋር የተለወጡ አሠራሮች እና

አስተሳሰቦችም ጭምር ጊዜ ሣይፈጅባቸው ተግባራዊ እንዲደረጉ የተጠናከረ የክትትልና የድጋፍ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡

1.23. መሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጡ በየደረጃው በሚገኙ አስፈፃሚ አካላት ክትትልና ግምገማ እየተደረገ ሊጠናከር እንደሚገባው የታመነ ነው፡፡ ይህንን አጠናክሮ በመገኘት ከወረዳ እስከዞን ያሉ የፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት መ/ቤቶች በውሎ ግምገማና በሣምንታዊ ስትሪንግ ኮሚቴ ስብሰባ ከሌሎች የበለጠ ተሞክሮ አላቸው፡፡ የአንጋጫና የጠምባሮ ወረዳ አቅም ግንባታ ጽ/ቤቶች በሚቀርቡ መረጃዎች መሠረት አፈፃፀምን በጋራ በመገምገምና ግብረ መልስ በመስጠት ከሌሎቹ ወደ ፊት የወጡ መሆናቸው በክትትል ተረጋግጧል፡፡ በዞን ደረጃም መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጡ በ3 ዙር ተገምግሞ በ2ዙር በስትሪንግ ኮሚቴ ተተችቶ ግብረ መልስ ተሰጥቷል፡፡

1.24. የሕዝብ ግንኙነት ሥራዎችን በሚመለከት የሥራና ከተማ ልማት የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ብሮሸር አዘጋጅቶ በማሠራጨት፣ በንግ ኢንዱስትሪ መምሪያ የመንገድ ደኅንነት የሥራ ሂደት የታሪፍ ደንብ በመግለጽ፣ የተሣፋሪዎችን መብትና ግዴታ በማሣወቅ አገልግሎቶችን በመኪና ውስጥና በመናኸሪያ ሥፍራዎች ለሕዝብ የማቅረብ ሥራ የሠሩ ሲሆን በፋ/ኢ/ል/ሴክተር የዞኑ የመረጃ ማሰባሰብና የማሠራጨት ሥራ ሂደት የዞኑን ሶሺዮ ኢኮኖሚ መረጃ የያዘ ብሮሸር ለማሠራጨት የቻለ ከመሆን ባሻገር በግብርናው ዘርፍ የሃደሮ ጡንጦ ዙሪያ ወረዳ ግ/ገ/ል/ጽ/ቤት በኤክስቴንሽን ሥራ ሂደት የአካባቢውን የዝንጅብል ምርት ለሃገር ውስጥ ገበያ ለማስተዋወቅ ያደረጋቸው ጥረቶች በአብነት የሚቀርቡ መሆናቸውን ከድጋፋዊ ክትትል መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

1.25. መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራ በሚደረግበት ወቅት የሚከሰቱ የለውጥ ተቃውሞዎችን በጥልቀትና በስፋት በመረዳት መሥራት እንደሚገባ ይታወቃል፡፡ በዚህ ረገድ እያንዳንዱ ሴክተር ስለለውጡ በቂ ግንዛቤ ያላቸውን፣ ስንፍና የማያጠቃቸውንና ለራሣቸውም ሆነ ለሕብረተሰብ እድገት ያለሙትን ራዕይ መተግበር የሚችሉትን ኃይሎች አዘጋጅቶ መጠቀም የግድ ስለሚል ይህንን ግንዛቤ ለመ/ቤቶች በድጋፋዊ ክትትል ወቅት ለማስገንዘብ በቂ ሥራ ተሠርቷል፡፡

1.26. በሙሉ ትግበራ ውስጥ ባሉ መ/ቤቶች በጥረት ተደራሽ ተደርገው የተጣሉ ግቦችን ከማሣካት አንፃር የተከለሰ እቅድ በማዘጋጀትና ቲም ቻርተር በመፈራረም ወደ ትግበራ በመግባት መ/ቤቶች እቅዶቻቸውን ማጠናቀቅ እንዲችሉ ተከታታይ

ክትትልና ድጋፍ የተደረገ ሲሆን በአሁኑ ወቅት አብዛኞቹ መ/ቤቶች ሪፖርቶቻቸውን በማቅረብ ላይ ይገኛሉ፡፡

1.27. ወደ ሙሉ ትግበራ በገቡ መ/ቤቶች እንደለውጥ የተገኙ ውጤቶችን በሚመለከት፣

- የጊዜ አጠቃቀም መሻሻል መጀመሩ
- የአመለካከት ለውጥ መታየት መጀመሩ
- የአገልጋይነት ስሜት እየዳበረ መምጣቱ
- ሥራዎች ከአንድ ማእከል ተጀምረው በዚያው የሚፈጸሙ ስለሆነ የአገ/ት አሰጣጥ መንዛዛት የቀነሰ መሆን/ፈፃሚዎች መወሰን መጀመራቸው/
- መረጃዎችና ውሣኔዎች በየሥራ ሂደቱ መሰጠት መጀመራቸው እንደለውጥ ከሚታዩ ውጤቶች ጥቂቶቹ መሆናቸውን ከድጋፋዊ ክትትል መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

II. መሠረታዊ የአሠራር ሂደቱ በመጠናቀቅ ላይ በሚገኙባቸው በ87 የዞንና የወረዳ መ/ቤቶች እየተተገበረ የሚገኘው የውጤት ተኮር ምዘና አፈፃፀም የተሣካ እንዲሆን የሁለት ዙር የባለሙያ ክትትልና እገዛ ተደርጐ በአንዳንድ መ/ቤቶች ለሠራተኞች ያልተሰጡ የግምገማ ነጥቦች በወቅቱ እንዲሰጡ የጋራ መግባባት ተደርጓል፡፡

የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራሞችን በተሣካ መልኩ ለመፈጸም የማስፈጸም አቅም ግንባታ ሥልጠና ወሣኝ በመሆኑ ለ291 አመራሮችና ከፍተኛ ባለሙያዎች ስለ መልካም አስተዳደር፣ ስለለውጥና ለውጥ አመራር፣ ስለማስፈጸም አቅም ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ 470 አመራርና ከፍተኛ ባለሙያዎች ሥልጠናውን በመሣተፍ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጓል፡፡ በአጠቃላይ በነዚህ በተደማመሩ ጥረቶች በመታገዝ ለአመቱ የታቀዱ የሪፎርም ሥራዎችን መሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናቱ ተጠናቆ ወደ ሙሉ ትግበራ በተገባባቸውና ጥናቱ በመጠናቀቅ ላይ በሚገኙባቸው መ/ቤቶች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ ተችሏል፡፡

III. **በገጠር ወረዳና ቀበሌ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ አፈፃፀም በተመለከተ፣**

ሕዝቡ በግልም ሆነ በጋራ የሚያከናውናቸውን ተግባራት አምኖ ብቻ እንዲሠራ እየተደረገ ያለው ጥረት አበረታች ነው፡፡ በዚህ አኳያ የቀበሌ መዋቅራችን በብዛኛው በግንባር ቀደም አርሶ አደር እንዲመራ ተደርጓል፡፡

ህ/ሰብን አሣምኖ የልማት እቅድን ለማስፈጸም በግማሽና ሩብ ዓመት አርሶ አደሩ ያቀደውን እቅድ እንዲፈትሽና እንዲከልስ ጠንካራ ክትትል ተደርጓል፡፡ ከአደረጃጀትም አኳያ ሕ/ሰቡ በልማት ቡድንና ደረጃ እቅዱን በጋራ እየገመገመ እንዲሠራ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡ ህ/ሰቡን አሣምኖ ወደ ልማት አቅጣጫ ለማስገባት የተለያዩ ሞዴሎችን መጠቀም ተገቢ በመሆኑ ሞዴል ግለሰቦችና መንደሮች በፓኬጁ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት ቅንጅታዊ አሠራር ለመፍጠር/በግብርና፣በጤና፣ በት/ትና ፍትህ አስተዳደር/ ጥረቶች የተደረጉ ሲሆን በየወረዳው የሞዴል ቀበሌ ፣ መንደርና ግለሰብ ብዛት በሚከተለው መግለጫ ተመልክቷል፡፡

| ተቁ | የወረዳው ስም | በረዳው ጠቅላላ ቀበሌ ብዛት | ሞዴል ቀበሌ ብዛት | ሞዴል መንደር ብዛት | ሞዴል ግለሰብ ብዛት በቁጥር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ወ | ሴ | ድ |
| 1 | ቀዲዳ ጋሜላ | 17 | 5 | 7 | 18 | 2 | 20 |
| 2 | ዳምቦያ | 17 | 5 | 7 | 10 | - | 10 |
| 3 | አንጋጫ | 17 | 5 | 6 | 16 | 1 | 17 |
| 14 | ዶዮገና | 13 | 5 | 6 | 10 | - | 10 |
| 5 | ጠምባሮ | 20 | 5 | 6 | 5 | - | 5 |
| 6 | ሃደሮ ጡንጦ | 14 | 5 | 6 | 14 | - | 14 |
| 7 | ቃጫ ቢራ | 21 | 5 | 2 | 3 | - | 3 |
| 8 | ጠቅላላ ብዛት | 119 | 35 | 50 | 76 | 3 | 79 |

የልማት እንቅስቃሴን ከመደገፍ አኳያ ሞዴል ግለሰብ፣ መንደርና ቀበሌን መርጦ የማሣወቁ ሥራ በሕብረተሰቡ ውስጥ የርስ በርስ የልማት ፉክክር ወይም የልማት ትግል ከአርሶ አደር ወደ አርሶ አደር ፣ ከቀበሌ ወደ ቀበሌ እንዲቀጣጠል ሁኔታዎችን አመቻችቷል፡፡

በዚህ በሞዴሎች አጠቃቀም ረገድ የተለያዩ መድረኮች በቀበሌያት ደረጃ እንዲፈጠሩ በማድረግ ሞዴሎችን እንደመሪ ምሣሌ ለማሣየት እየተቻለ ህብረተሰቡን ለልማት ለማንቀሣቀስ ጥረት እየተደረገ ስለሚገኝ የሕዝቡም ተነሣሽነት ካለፉት ጊዜያት በተለየ መልኩ ለውጥ እየታየበት መጥቷል፡፡ የተለያዩ የኅ/ሰብ ኮንፍራንሶችን በመፍጠርና መድረኮችን በማዘጋጀት አርሶ አደር ተኮር እቅድ እንዴት መዘጋጀት እንዳለበት ከዚያም በመከለስና ውጤቱን ተመልሶ ራሱ እንዲገመግም አስፈላጊ መሆኑና ጥቅሙንም አውቆ

እንዲሠራ በ119 የገጠር ቀበሌ ትምህርት ተሰጥቶ ኅ/ሰቡ እቅዱን ከግለሰብ ጀምሮ እስከ ልማት ቡድን ድረስ መገምገም የሚችልበት ሥርዓት እንዲጠናከር ተደርጓል።

ተሣትፎ በዋነኛነት በግል ሥራ ያተኮረ እንዲሆን ህ/ሰቡ ለግል እንቅስቃሴው ሰፊውን ጊዜ 80% መጠቀም እየቻለ ቀሪውን 20% ለጋራ ተሣትፎ መዋል እንዲችል እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች አበረታች ውጤቶች እየታየባቸው ይገኛሉ። የለውጥ ጅምሮችም በመታየት ላይ ናቸው። በተጨማሪም በጋራ ሥራዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሣተፍ ከማድረግ አኳያ ኅ/ሰቡ በሣምንት አንድ ቀን በመንገድ ሥራ ፣ በሽንት ቤት ቁፋሮ፣ በምንጭ ጠረጋና በሌሎችም የልማት ሥራዎች እንዲሣተፍ ክትትልና ድጋፍ በመደረግ ላይ ይገኛል።

የተሣትፎ መድረክን በስፋት በመፍጠር ኅ/ሰቡ በፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማኀበራትዊ ጉዳዩች በራሱ መድረክ ፈጥሮ ተሣትፎን በማጐልበት ላይ ሲሆን ለምሣሌ፣ በዳምቦያ ወረዳ የመገሬ ቀበሌ ሕዝብ በራሱ ተነሣሽነት መድረክ አዘጋጅቶ ውይይት በማድረግ ት/ቤት ሠርቶ መጠቀም መጀመሩ፣ የሃደሮ ጡንጦ ዙሪያ ወረዳ የሆማ ቀበሌ ሕዝብ በራሱ ጊዜ ተነሣሥቶ ለተለያዩ ለመሠረተ ልማት ሥራዎች ዝርጋታ የሚያግዙ ተግባራትን በማካሄድ ላይ መገኘቱ፣ እንዲሁም የሆማና የመንደዬ ቀበሌ ሕዝብ የቀበሌው ንብረት የሆነውን ደንና ሣር አለአግባብ የሚጠቀሙ ግለሰቦችን በራሱ መድረክ የማጋለጥ ሥራ እየተሠራ መገኘቱና በቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ፣በሸሸራ ቸፌ ቀበሌ የሞዴል በዓል መከበሩ የሚጠቀሱ ተግባራት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በልማት እቅድ ውሣኔዎች ላይ ኅ/ሰቡን ማሣተፍ የሚያስችል ሁለንተናዋ ተሣትፎ ለማሣደግ ከላይ በተጠቀሱ እንደሆማ ባሉ ቀበሌዎች የአኘል ምርትን ለማስፋፋት አርሶ አደሮች የርስ በርስ ልምድ ልውውጥ በማድረግ የራሣቸውን ውሣኔ በማዳበር የልማት ሥራዎችን ያካሂዳሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ የእቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ለማጠናከር በዞኑ ውስጥ በ119 የገጠር ቀበሌ የኢንስፔክሽን ቡድን ተቋቁሞ ተገቢውን ድጋፍ በመስጠት ላይ ይገኛል። ባለጉዳይን በቀጠሮ የማመላለስ አሠራር እንዳይኖርና ሣይጉላላ ፈጥኖ ምላሽ ከመስጠት አኳያ የሥራ አስኪያጆች ቅጥር ከተፈጸመ ወዲህ ለውጥ በመታየት ላይ ይገኛል። በየደረጃው ለሕ/ሰብ በሚሰጡ አገልግሎቶች ቅር የተሰኘ ዜጋ የተፈጠረውን ችግርና እርካታ ያላስገኘ ጉዳዩን ለይቶ ቅሬታውን በተዘጋጁ በእርካታ መመዘኛ ቅፃ ቅፆችና በመዛግብት ጭምር አስተያየት መስጠት የሚቻልበት አሠራር ተዘርግቶ ድጋፍ እየተደረገ አካሄዱ እንዲጠናከር በመደረግ ላይ ይገኛል።

የሕዝብ ፍላጐትና ቅሬታውን ለመለየት በዋናነት ሕዝቡ በስብሰባዎች፣ በኮንፍራንሶች፣ በጉባዔዎችና በሌሎችም የውይይትና የምክክር መድረኮች ሣይሸማቀቅ የሚሰጣቸው አስተያቶች በግብዓትነት እየተያዙ የሕዝብን ፍላጐትና ቅሬታ ለይቶ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን የሚደረጉ ጥረቶች በተለይም በቀሌያት ደረጃ በስፋት እንደቀጠሉ ድጋፋዊ ክትትል ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

*የተጠያቂነትና ግልጸኝነት አሠራርን በማስፈን ረገድ፣*

- በውሣኔ አሰጣጥ የእቅድ አፈፃፀም እንዲሁም ሕግ፣መመሪያና አሠራርን በተመለከተ ለሕዝብ በጊዜ የማሣወቅና የዝግጅት ጊዜ ገደብ አሠራር ተዘርግቷል፡፡ ለምሣሌ የግብዓት እዳና የግብር አሰባሰብ በ119ኙ የገጠር ቀበሌ በጋራ የሚወሰን መሆኑ
- ህዝቡ በመደበኛ ኘሮግራም የራሱን እቅድ እንዲገመግም ይደረጋል፡፡ ለምሣሌ በየሩብ ዓመቱ የእቅድ ግምገማና ክለሣ መደረጉ፣
- ከእቅድ ዝግጅት ጀምሮ እስከ አፈፃፀሙ ድረስ ተጠቃሚው ኅ/ሰብ እንዲያውቅና እንዲሣተፍ በ119ኙ የገጠር ቀበሌ በም/ቤት ተወስኖ ለኅ/ሰቡ እንዲታወጅ ይደረጋል፡፡

**ከአደረጃጀት አንፃር፡**

- በ119 የገጠር ቀበሌ እና በ7 የገጠር ወረዳ የቀበሌ አደረጃጀት በቀበሌ አመራርና በመንደር ተወካዮች ጋር በመሆን ሕዝቡን በቀጥታ በማግኘት የልማት እቅዳቸውን በመፈጸም ላይ ይገኛሉ፡፡
- በ7 የገጠር ወረዳ በሚገኙ በ119 ቀበሌዎች አራቱ ኮሚቴዎች በሚገባ ተደራጅተው በቅንጅት እየሠሩ የሚገኙ መሆኑን በድጋፋዊ ክትትል ወቅት የተሰበሰቡ መረጃዎች ያመለክታሉ፣

በአጠቃላይ በመልካም አስተዳደር ፓኬጆች ፣አዋጆችና መመሪያዎች አፈፃፀም መልካም ተሞክሮዎችን ለማስፋት ኅ/ሰቡን በግልና በጋራ አሣምኖ ለማሠራት ለ3213 የገጠር ወረዳ ቀበሌ አመራሮች አጫጭር ሥልጠናዎችን በመስጠት አቅማቸውን ለመደገፍ ታቅዶ 1909 ተሣታፊዎች ዴሞክራሲያዊና ልማታዊ በሆነ አሠራር ግንዛቤ እንዲጨብጡ ጥረት የተደረገ ከመሆን ጋር አንድ የምርጥ ተሞክሮ ቅመራ ሠነድ ተዘጋጅቶ ለክልሉ አቅም ግንባታ ቢሮ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

በ119 የገጠር ቀበሌ የሚገኙ ሥራ አስኪያጆች በቀበሌ ደረጃ የሚገኘውን የአስተዳደር እርከን በብቃት ለመከታተል የሚያስችላቸውን የመሪነት ሚና፣ የእቅድ ዝግጅት፣ የፋይናንስና ንብረት አያያዝ፣ የመልካም አስተዳደርና የመረጃ አደረጃጀት ሥልጠና እንዲሰጣቸው ታቅዶ

ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አራት ሥራ አስኪያጆች ሣይሣተፉ የቀሩ ቢሆንም እቅዱ በተሣካ መልኩ ተግባራዊ ሆኗል፡፡

*IV. የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም በተመለከተ፣*

1. የዞኑን የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም ከማሣካት አንፃር የዞኑ ፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ በዞኑ ውስጥ በሚገኙ በፍትህ ተቋማት የሚታዩ ችግሮችን ለይቶ በመያዝ፣
   1.1. በዞኑ ውስጥ ትልቅ ችግር ሆኖ በቆየው በበጀት እጥረት ላይ ዞናዊ ውይይት ተርጎ ውሣኔ ማስተላለፉና ተግባራዊ መደረጉ
   1.2. በፍትህ ተቋማት ቅንጅታዊ አሠራር እንዲለመድ ብርቱ ጥረት መደረጉና ተግባራዊ መሆን መጀመሩ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡
2. የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም በእቅድና በሪፖርት እንዲመራ በማድረግ ረገድ
   2.1. በእያንዳንዱ ወረዳ የሚገኙ አስተባባሪ ኮሚቴዎች እቅድ አዘጋጅተው የሚንቀሣቀሱ ሲሆን ለአብነት የጠምባሮ፣ የአንጋጫና የቀዲዳ ጋሜላ ወረዳዎች ተጠቃሽ ይሆናሉ፣
   2.2. በየሩብ ዓመቱ ባይሆንም የዘጠኝ ወራት ሪፖርት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፣
   2.3. በፍትህ ተቋማት አፈፃፀም ላይ በሚያጋጥሙ ችግሮች ዙሪያ ለ132 የተቋማቱ አመራርና ባለሙያዎች የሥልጠናና የውይይት መድረክ በዞን ማእከል ለማዘጋጀት ታቅዶ በግንቦት ወር 2001 በተካሄደው መድረክ 85 አመራሮችና ባለሙያዎች በሥልጠናው ተሣታፊ ሆነዋል፡፡ ይህንኑ መድረክ ወደ ወረዳዎች ተደራሽ ለማድረግ በተደረገው ጥረት በጠምባሮና በዳምቦያ ወረዳዎች 295 አመራሮችንና ባለሙያዎችን ያሣተፈ የጋራ መድረክ ሊካሄድ ችሏል፣
   2.4. ለ890 የመንግስት ሠራተኞችና ለተለያዩ የኅ/ሰብ ክፍሎች ስለፍትህ ሥርዓቱ ያላቸውን ግንዛቤ ለማዳበር የጋራ መድረክ ከዞን እስከ ወረዳዎች ለመፍጠር ታቅዶ ለ1050 ለተለያዩ የኅ/ሰብ ክፍሎች ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ተሠርቷል፡፡ የቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት ከወረዳው አቅም ግንባታ ጽ/ቤት ጋር በመሆን የሁለት ዙር ሥልጠናዎችን በበቂ ሎጀስቲክ አስደግፎ ለመስጠት በመቻል የጐላ ተጠቃሽነትን አትርፏል፡፡

3. የፍትህ ተቋማቱ በጣምራና በተናጠል እንዲጠናከሩ በተደረገው አሠራር የተገኘውን ለውጥ ከመገምገም አንፃር ተቋማቱ ለኀ/ሰቡ ተደራሽ አገልግሎት መስጠት መቻላቸው እንደለውጥ ተመዝግቧል፡፡

## 2/ በፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ንዑስ ኘሮግራም

1. የፍርድ ሂደት ቀልጣፋ ለማድረግ
   - ፎርማቶችን በመጠቀም መሥራት መጀመሩ ፣
   - የችሎት ሥራዎችን ከፋፍሎ መሥራትና ማደራጀት መቻሉ፣
   - በአንድ ጊዜ ከሁለት እስከ ሶስት ችሎት የመሰየም አሠራር መጠናከሩ ፣
   - ተዘዋዋሪ ችሎቶችን ተደራሽ ለማድረግ በመቻሉ ፡ ዞን በ6 ወረዳ ማዕከል 7ቱ የገጠር ወረዳዎች በ7 ንዑሣን ጣቢያዎች አገልግሎት መስጠት መቻላቸው፣
   - ዘመናዊ የጽህፈት መገልገያ መሣሪያዎችን ለ3 ወረዳዎች በእርዳታ በስጠትና ሌሎችም እንዲገዙ መደረጉ፣
   - የይግባኝ ቅሬታዎችን በወቅቱ ገልብጦ ለመስጠት የፎቶ ኮፒ ማሽኖችን በመግዛት ማደራጀት መቻሉ
   - ለተዘዋዋሪ ችሎት ሥራ የአበልና ነዳጅ በጀት እንዲመደብ በመደረጉ ቀልጣፋ የፍርድ ሂደት እንዲጠናከር ሁኔታዎች እንዲመቻቹ ተደርጓል፡፡
2. በይግባኝ ክርክር ይግባኝን ገልብጦ በመስጠት ለተገልጋዩ ያስገኘው ለውጥ ቀደም ሲል ረጅም ጊዜ ይፈጅ የነበረው ይግባኝን ገልብጦ የመስጠቱ ሂደት በአሁኑ ወቅት በዞንና በወረዳ ፍ/ቤቶች የፎቶ ኮፒ ማሽኖች ተገዝተው በመሰጠታቸው ችግሩ በእጅጉ ተቀርፏል፡፡
3. የፍርድ ጥራት ለመለካት የተቀመጡ አመልካቾችን በመጠቀም የፍርድ ጥራት ለመለካት እየተሞከረ መሆኑን መረጃዎች የሚያሣዩ ሲሆን ለምሣሌ የተወሰነ ውሣኔ በይግባኝ መሻር አለመሻሩ አንዱ ሲሆን በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ደረጃ ከተወሰኑ ውሣኔዎች 90% በይግባኝ የጸኑ መሆኑ በድጋፋዊ ክትትል ተረጋግጧል፡፡
4. ምርጥ የፍርድ ውሣኔዎችን ከማስፋት አንፃር ለአብነት እጅ ከፍንጅ በሚያዙ ወንጀለኞች ላይ በአንድ ሰዓት ከአርባ ስምንት ደቂቃ ውስጥ ውሣኔ የተሰጠበትን ጉዳይ ለሌሎች ተሞክሮውን የማስፋት ሥራ በመሥራት ላይ መገኘቱ ተጠቃሽ ነው፡፡
5. የጉዳዮችን ክምችት ለመቀነስ በተደረገው ጥረት 6989 መዛግብት ከዞን እስከ ወረዳ ውሣኔ አግኝቷል፡፡

6. 355 መዝገቦች በወረዳዎች ደረጃ የሰው ኃይል እጥረት በማጋጠሙ ምክንያት ውሣኔ ሣያገኙ ቀርተዋል፡፡
7. የሥነ ምግባር መከታተያን በሚመለከት በሥነ ምግባር ጉድለት በ2 ዳኞች ላይ እርምጃ ተወስዶ ከዳኝነት ሥራቸው ላይ ተነሥተዋል፡፡
8. በተቋሙ ለመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የሰው ኃይል ተደልድሎ የሥራ ቦታ በመመቻቸት ላይ ይገኛል፡፡

### 3/ በዐቃቤ ህግ ማሻሻያ ንዑስ ኘሮግራም

1/ የፖሊስና የዐቃቤ ህግ የጋራ ሥራ በሚመለከት በከባድ ወንጀሎች የምርመራ ሂደት በጋራ የመሥራት ልምዱ በመዳበር ላይ እንደሚገኝ የክትትል መረጃዎች ያመለክታሉ፡

2/ ለምሥክሮች አበል ስለሚከፈል በማስረጃ አቀራረብ የተፈጠረ ችግር የለም

3/ በ1998 እና በ1999 በጀት ዓመታት በአራት አቃቤ ህጎች ላይ ክስ ተመስርቶ የገንዘብ ቅጣት እርምጃ በመወሰዱና ከቦታ እንዲነሱ በመደረጉ ለውጥ የተገኘ መሆኑን በድጋፋዊ ክትትል ወቅት የተሰበሰቡ መረጃዎች ያስረዳሉ፡

4/ የጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥ የክልል ሥልጣን ቢሆንም በውልና ማስረጃ በማነበራት ምዝገባ ከዞን እስከ ወረዳ ድረስ መሟላት የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በግልጽ በመለጠፍ እየተሠራ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

5/ የማኅደር አያያዝ ዘመናዊ ባይደረግም የተፈለገውን መረጃ ወዲያው ለማግኘት በሚያስችል መልኩ የተደራጀ መሆኑ በአካላዊ ምልከታ ተረጋግጧል፡፡

6/ ለ13509 ለተለያዩ የኀ/ሰብ ክፍሎች የንቃተ ህግ ት/ት እንዲሰጥ ከባለሙያው መ/ቤት ጋር አብሮ ለመሥራት ተችሏል፣

7/ አራት በሃሰት የመሰከሩ ግለሰቦች ተከሰው ወደ ህግ ፊት ቀርበው ጉዳያቸው በሂደት ላይ እንደሚገኝ የክትትል መረጃዎች ያስረዳሉ፣

8/ በኦፊሰር መደቦች ላይ የሰው ኃይል ባለመመደቡ በሥራው ላይ ተጽእኖ በማሣደር ላይ እንደሚገኝ በድጋፋዊ ክትትል ወቅት ከተካሄው ውይይት ለመረዳት ተችሏል፣

9/ ለመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ መ/ቤቱ የሥራ ቦታ በማመቻቸት ላይ ይገኛል፡

### 4/ በፖሊስ ማሻሻያ ንዑስ ኘሮግራም

1. በዞኑ ውስጥ በአንድ የከተማ አስተዳደር በ7 የገጠር ወረዳ የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ት/ት በተሻለ ጥራትና እንቅስቃሴ በመስጠት ላይ መገኘቱን ከባለሙያ መ/ቤት የሚቀርቡ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

2. በዚሁ መሠረት ት/ቱ በሁለት የት/ትና የሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች፣ በ129 ቀበሌዎችና ከ1042 በላይ በሆኑ ጉጦች ኮሚቴ ተደራጅቶና የአሠራር ግንዛቤ ተፈጥሮ በተጠናከረ መልኩ በመሠራት ላይ ይገኛል፣ ለምሣሌ፡- የዞኑ የወንጀል መከላከል የሥራ ሂደት በዞኑ በሞዴልነት በተያዙ በአንጋጫ ወረዳ በሺኖ ፉነሙራና በዶዮገና ወረዳ በዲኒቃ ቀበሌዎች በአካል በመገኘት ኮሚቴ ማቋቋም መቻሉ ተጠቃሽ ተግባሮች ናቸው፡፡
3. የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ት/ት በመሰጠቱ የተገኙ ውጤቶች
    - ህ/ሰቡ ከፖሊስ ጋር ወንጀልን አምርሮ መታገል መጀመሩ ፣
    - የወንጀል ድርጊት መቀነስ መቻሉ፣
    - በየወረዳው ጊዜያዊ ማቆያ ጣቢያዎች ባዶ መሆን፣
    - ለፖሊስ መረጃ የመስጠት ልምድ እየዳበረ የመጣ መሆኑና ዘረፋ ሙሉ በሙሉ መቆሙ፣
    - ስርቆት ሙሉ በሙሉ መቆሙ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡
4. የተሣተፉ የኅ/ሰብ ክፍሎች በሚመለከት አርሶ አደሮች ፣ተማሪዎች ፣ ወጣቶችና ሌሎች በድምሩ 254882 ዜጐች መሣተፋቸውን በድጋፋዊ ክትትል ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
5. በኮሚኒቲ ፖሊሲንግ የተሠሩ ዋና ዋና ሥራዎች
    - ኅ/ሰቡ ወንጀልን እንዲጸየፍ ግንዛቤ መፍጠር
    - የወንጀል አስከፊነት እንዲረዳ ማስተማር
    - ኅ/ሰቡ ከፖሊስ ጋር ተባብሮ እንዲሠራ ማድረግ ናቸው፡፡
6. በልዩ ተሞክሮ የተገኘ የወንጀል መከላከል ሥራ በሚመለከት ኅ/ሰቡ ወንጀለኞችን በሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ ዘዴ ማሰሮ ተዘጋጅቶ ተጠርጣሪን በጽሁፍ የማጋለጥ ሂደት በአንዳንድ ቀበሌዎች ውጤታማ መሆን መቻሉ ምሣሌ፡ / የቡ ቀበሌ በዳምቦያ ወረዳ/ ተጨማሪ የሰው ኃይል ከማዘጋጀት አንፃር ዞኑ ለፌዴራል ፖሊስ 34፣ ለልዩ ኃይል 80፣ ለመደበኛ ፖሊስ 34 እና ለእጩ መኮንንነት 20 በድምሩ 168 እጩዎችን አዘጋጅቶ በመላክ ተግባሩን በመወጣት ላይ መገኘቱን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## 5/ ከምክር ቤቶች ማሻሻያ አንፃር

1/ እቅድ ክንውን ለመገምገም በተያዘው መርሃ ግብር መሠረት ከ3 መደበኛና ከአንድ አስቸኳይ ጉባዔዎች መካከል ሁለት መደበኛ ጉባዔዎች ተካሂደዋል፡፡ የወረዳዎች ጉባዔ በሚመለከት በ4 ዙር መካሄድ ከሚገባቸው መካከል 3ቱ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ድረስ መከናወናቸውን የክትትል መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡

2/ የም/ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች በተመረጡ መ/ቤቶች በ2 ዙር በመገኘት የአፈፃፀም ግምገማ ካደረጉ በኋላ ግብረ መልስ በመስጠት የመ/ቤቶቹን አፈፃፀም ለመግለጽ በቂ ጥረት መደረጉ ተረጋግጧል፡፡

3/ የዞኑ ም/ቤት የጉባዔ ውሣኔዎች በበጀት አመቱ ሁለት ጊዜ ተዘጋጅተው የተሠራጩ ሲሆን ከዚሁ ጋር የተሻሻለው የአባላት የሥነ ምግባር ደንብ ለ93 የም/ቤቱ አባላት እንዲዳረስ መደረጉ ም/ቤቱ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ከማስተዋወቅ አንፃር የተሻለ ተሞክሮ መኖሩን ያሣያል፣

4/ የዱራሜ ከተማ አስተዳደር ጨምሮ የ7ቱም ገጠር ወረዳ ም/ቤት አፈ ጉባዔዎችና ዋና አስተዳዳሪዎች በሶስቱም የመንግስት አካላት አንድነትና ልዩነት ላይ የሥልጠና ርዕስ ተዘጋጅቶ ለአባላት ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ መሠራቱ ለም/ቤቱ ጥንካሬ መገለጫዎች ናቸው፣

5/ የም/ቤቱን ሥራዎች የበለጠ የሚያጠናክር የልምድ ልውውጥ በወረዳዎች ደረጃ በበጀት ዓመቱ 2 ጊዜ የተደረገ ሲሆን የዞኑን ም/ቤት ከወላይታ ዞን ም/ቤት ሰኔ 2 ቀን 2001 ዓ/ም 26 አባላት የሚገኙበት ቡድን የልምድ ልውውጥ ለማድረግ መምጣቱ የም/ቤቱ አሠራር በተሻለ እንቅስቃሴ ውስጥ ለመገኘቱ ማስረጃ ሲሆን ከዚህ ጋር ተያይዞ ም/ቤቱ ሚኒ ላይብረሪ አዘጋጅቶ አባላትና ሠራተኞች በትርፍ ጊዜያቸው ጭምር እንዲጠቀሙ መደረጉ እንደ ልዩ ተሞክሮ ከመሆኑም ባሻገር ከዚህ በፊት ሲንጠባጠብ የነበረው የቀበሌ ም/ቤት ከሞላ ጎደል በተሻለ ሁኔታ በሁሉም ቀበሌዎች ጉባዔ ይካሄዳል፣ በዞንና በወረዳ መ/ቤቶች ቅንጅት በክላስተር ደረጃ የም/ቤት አባላት በመልካም አስተዳደር ዙሪያ የመወያየት ጅምር ተሞክሮዎች አሉ፡፡

### 6. *በማረሚያ ቤቶች ማሻሻያ ንዑስ ኘሮግራም*

1/ የታራሚዎችን ሰብዓዊ መብት ከመጠበቅ አኳያ የወንድና የሴት ታራሚዎች የተለየ ግቢ ያለ ቢሆንም የእስረኞች ቁጥር ወደ 611 በመድረሱ የቦታ ጥበት ተከስቷል፡፡ ማረሚያ ቤቱ ችግሩን ለጊዜው ለማስተንፈስ የኮሚቴ ቢሮዎችንና የሻይ ክበብ ቤቶችን ጭምር የማስለቀቅ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በመጠቀም እስረኞችን በአግባቡ ለመያዝ ጥረት መደረጉ ለአብነት ከሚጠቀሱ ተግባሮች አንዱ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ለ611 ታራሚዎች የህግ ፣የቀለም፣የሙያና የግብረ ገብ ት/ት በተለያዩ ባለሙያዎች እንዲሰጥ መደረጉን በድጋፋዊ ክትትሉ ወቅት የተያዘው መረጃ ያሣያል፡፡

2/ እስረኞችን በወንጀል ክብደትና ቅለት ለይቶ በተለያየ ዞን ማቆየት ተገቢ ቢሆንም ተቋሙ ሲመሠረት በዚህ ኘላን ታስቦ የተሰራ ባለመሆኑ ለከባድ ወንጀለኞች የተለየ ክትትል በማድረግ ሁኔታዎች በትኩረት ውስጥ እንዲሆኑ ጥረት የተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

3/ የታራሚ መኖ አቅርቦት በጋዜጣ ማስታወቂያ ተጫራች ቀርቦ እንደሚፈጸም፣ የታራሚ ኮሚቴ እንደሚሣተፍ፣ ተለዋዋጭ አባላት በኮሚቴነት እንደሚሠሩ ፣እህሉን የተቋሙ ንብረት ክፍል እንደሚረከብና በጠቃላይ የተሻለ የክትትል ሥርዓት ተዘርግቶ አሠራሩ በመፈጸም ላይ እንደሚገኝ ከተቋሙ ጋር ውይይት በተደረገበት ወቅት የቀረቡ ማስረጃዎች ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ናቸው፡፡

4/ ማረሚያ ቤቱ ለታራሚዎች የቀለም ት/ት ለመስጠት የወሰደው እርምጃ እና የተገኘው ውጤት በአብነት የሚጠቀስ ነው፡፡ በተለይም በክልሉ ካሉት ማረሚያ ቤቶች የመንግስት ቅጥር መምህራን ተመድበውለት እስከ 8ኛ ክፍል ታራሚዎችን ማስተማር መቻሉ ሊበረታታ የሚገባ ተግባር መሆኑን ከተደረገው ድጋፋዊ ክትትል ግንዛቤ ለመጨበጥ ተችሏል፡፡

የማስፈጸም ክፍተት ከመለየትና መረጃ ከማዘጋጀት አንፃር ወጥ የሆነ በማኑዋል ደረጃ የባለሙያ ጥናት ባይደረግም የዞንና የወረዳ አቅም ግንባታ ጽ/ቤት ባለሙያዎች ባደረጉት ድጋፋዊ ክትትልና ግምገማ መረጃ መሠረት ፣

- በፋይናንስ ሴክተር የግዥና ክፍያ አሠራር መጓተት ያለበት መሆኑ
- መ/ቤቶች የተገልጋይ እርካታ ምዘና ጥናትና መረጃ አለማደራጀት መታየቱ
- አልፎ አልፎ በአመራሩና በፈፃሚው ደረጃ ለሥራዎች የባለቤትነት ስሜት ያልተጠናከረ መሆን
- ከሠራተኞች ምደባና ዝውውር ጋር የተያዙ ችግሮች
- የስታንዳርድ አጠቃቀም ግንዛቤ አለመዳበር
- ተከታታይ የአፈፃፀም ግምገማ ውይይቶች ተጠናክረው አለመቀጠልና ደካማ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት መታየት ውስን የተለዩ ችግሮች ብቻ ነበሩ፣

3/ ያልተከናወኑ ቁልፍ ተግባራት

3.1. ለዞንና ለወረዳ የኢንስፔክሽን ቡድን አባላት በድምሩ ለ54 አባላት ሊሰጥ የታቀደው የግንዛቤ ማስጨበጫና የውይይት መድረክ አለመካሄድ

7/ በዞኑ ICT እንዲስፋፋ በማድረስ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍንና ቀልጣፋና ተደራሽ የሆነ አገ/ት አሰጣጥ እንዲፈጠር ተቋማትንና ሕ/ሰቡን የዘመናዊ መረጃ ልውውጥ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ፣

- ለ100 ከዞን ሴ/መ/ቤቶች ለተውጣጡ ሠራተኞች መሠረታዊ የኮምፒውተርና የኢንተርኔት አጠቃቀም ስልጠና ለመስጠት በተያዘው እቅድ መሠረት ማኑዋል ተዘጋጅቶ በአሁኑ ወቅት በዞኑ ማዕከል ያሉን ኮምፒውተሮች 7 ብቻ ስለሆኑና የሠልጣኞች ብዛት 63 በመሆኑ ምክንያት ሰልጣኞቹን በሦሥት ቡድን በማካፈል በየቡድኑ 21 ሰልጣኞች ማለትም በአንድ ኮምፒውተር 3 ሰው በመመደብ በዞን ማዕከል እየሠለጠኑ ይገኛሉ፡፡ በተመሣሣይ መልኩ በቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ 30 ሠልጣኞች ፣ በቃጫ ቢሮ ወረዳ 47 ፣ በዱራሜ ከተማ አስ/ር 13 ሰልጣኞች በድምሩ 90 ሲሆን የዞን ማዕከልና የወረዳዎች በድምሩ 153 ሠራተኞች እየሠለጠኑ ይገኛሉ፡፡ ሆኖም በአሁኑ ወቅት ያለው የመብራት መቆራረጥ ከፍተኛ ተጽዕኖ በማሣደር ላይ ይገኛል፡፡ በተቀሩት አዳዲስ ወረዳዎች ላይ በከፍተኛ ደረጃ የኮምፒውተርም ሆነ በኢኮቴ ሥራ ዘርፍ የሠለጠነ የሰው ኃይል የላቸውም፡፡
- በዞኑ በሚገኙ የመንግሥት መ/ቤቶች ያለውን የኮምፒውተር ብዛት ለመለየትና በተቻለ መጠን የዘመናዊ መረጃ ልውውጥ ተጠቃሚ ለማድረግ የየሴክተሩን የሰው ኃይልና የኮምፒውተር አጠቃቀም ክፍተት ለማጥበብ ከክልል በእርዳታ የተሰጡትን 27 ስካነሮችና 5 ኮምፒውተሮች ለወረዳዎች ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እንዲሠራጭ ተደርጓል፡፡
- አርሶ አደሩን የገበያ መረጃና ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለማድረግ ይቻል ዘንድ በዞናችን ከሚገኙት 119 የገጠር ቀበሌያት መካከል 65 ወይም 54% ያህሉ የሽቦ አልባ ስልክ አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ከነዚህም ውስጥ 2% የሚሆኑት የመብራት አገ/ት ጭምር ተጠቃሚ ናቸው፡፡
- የጥገናና ቪዲዮ ኮንፍረንሲንግ አገልግሎትን በሚመለከት በአንዳንድ የወረዳ አቅም ግንባታ ጽ/ቤቶች ለምሣሌ፣ በቀ/ጋ/ወረዳ 2 ኮምፒውተሮችን ፣ በጠምባሮ ወረዳ የፎቶ ኮፒ ማሽንና 1 ኮምፒውተር ቀላል ጥገና ተደርጐላቸዋል፡፡ ከዞን መ/ቤቶች ከተሰበሰበው መረጃ 26 ኮምፒውተሮች መለስተኛ ወይም ከፍተኛ ጥገና የሚያስፈልጋቸው ሲሆኑ እነዚህን ለመጠገን በዋናነት የሚያስፈልጉ

ሶፍትዌሮች /Resource CDዎች እና በአጠቃላይ የጥገና ማእከል ባለመኖሩ ሥራው የታቀደውን ያህል እንዳይተገበር ምክንያት ሆኗል፡፡

- በዞኑ የተቋቋመው የመረጃ ማዕከል በጉጉታ ኬር ልማት ማኅበር የሚተዳደር ሆኖ በዞን አቅም ግንባታ የኢኮቴ ሥራ ሂደት የሚደገፍና ክትትል የሚደረግበት ሆኖ ማዕከሉ ለአካባቢው ሕ/ሰብና ለመንግስት ሠራተኞች የመረጃ ምንጭ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል፡፡
- የከምባታ ማኅ/ሰብ ሬዲዮ ጣቢያ ግንባታ 98% ሥራው የተጠናቀቀ ሲሆን በአሁኑ ወቅት የሥራ አስኪያጅና የጥበቃ ቅጥር ተፈጽሞ የቀሪ ሥራዎች አጨራረስና የቀጣይ ኘሮግራሞች አተገባበር ዝግጅት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

8/ አዲሱን መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ በአግባቡ ለመተግበር ይቻል ዘንድ የክልሉና የዞኑ አቅም ግንባታ መምሪያ በቅንጅት 16 የተለያዩ የሥልጠና ማዕከላትን በዞን ደረጃ በማዘጋጀት ለተለያዩ የሥራ ሂደቶች ከ15 — 26/06/2001 ዓ/ም ድረስ ባሉት ቀናት ሥልጠና በመስጠት ሰፊ የማብቃት ሥራ ተሠርቷል፡፡ በዚህም ሥልጠና መሰልጠን ከሚገባቸው 1496 ሠራተኞች መካከል ወንድ 957 ሴት 142 በድምሩ 1099 ሠልጣኞች በ34 ወንድ አሰልጣኞች በመሰልጠን ወደ ሙሉ ትግበራ ተገብቷል፡፡

- ከዚህም በተጨማሪ በክልሉ አቅ/ግን/ቢሮ የሰው ኃብት ልማት ዋና የሥራ ሂደት አዋሣ ላይ ባዘጋጀው የአሰልጣኞች ሥልጠና ላይ ከዞን አቅ/ግን/መምሪያ ፣ከዱ/ከ/አስተዳደርና ከ7ቱ የገጠር ወረዳ አቅ/ግን/ጽ/ቤቶች ዋናና ም/ኃላፊዎችን ጭምር የሰው ኃብት ልማት የሥራ ሂደት ባለሙያዎች በድምሩ 24 አሰልጣኞች ሰልጥነው ከተመለሱ በኂላ በዞንና በየወረዳዎቹ በየደረጃው የሚገኙ አመራሮችና ባለሙያዎችን እንዲሁም የተለያዩ የኅ/ሰብ ክፍሎችን ያካተተ ሥልጠና በተለያዩ ወቅቶች ሠጥተዋል፡፡ ስልጠና ከተሰጠባቸው ርዕሶችም ዋና ዋናዎቹ በመልካም አስ/ር ምንነትና መርሆዎች፣ በማስፈፀም አቅም ግንባታ ምንነት፣ በመረጃ አያያዝ፣ በእቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም መሠረታዊ ጽንሠ ሀሣብ ፣ በለውጥና የለውጥ ሥራ አመራር ፣ በፍትህ ሥርዓት አተገባበር ፣ በግንኙትና በሌሎችም ተመሣሣይ ርዕሶች ጭምር ተሰጥቷል፡፡
- የሥልጠና ፍላጐት ዳሰሳና ድጋፋዊ ክትትል ለማድረግ በተካሄደው አካላዊ ምልከታ ከዞንና ከወረዳ መ/ቤቶች ፣ከዱራሜ ሆስፒታል፣ ከዱራሜ ኢንደስትሪያል ኮሌጅን ጨምሮ በ2ኛው ዙር የሥራ ምደባ አግኝተው ሥልጠና ያልወሰዱ ወንድ 108 ሴት 64 በድምሩ 172 ሠራተኞች ሥልጠና

የሚያስፈልጋቸው መሆኑን በተደረገው የሥልጠና ፍላጉት ዳሰሳ መረጃ ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡

- የውጭ ሃገር ትምህርት እድልን በሚመለከት፣ በግል በመፃፃፍ የት/ት እድል ላገኙት ለአቶ ዮሃንስ ሎበንጐ የከምባታ ጠምባሮ ዞን ግ/ገ/ል/መምሪያ ባለሙያ ድጋፍ እንዲሰጣቸው ባቀረቡት መሠረት ለክልሉ አቅ/ግን/ቢሮ የመገጣጠሚያ ድጋፍ ደብዳቤ ተሰጥቷቸዋል፡፡
- ለሃገር ውስጥ ት/ትና ሥልጠና በአርባን ኢንጂነሪንግ ፣በሕግ፣በፐብሊክ ፋይናንሻል ማናጅመንት ፣ በደቨሎኘሜንታል ኢኮኖሚክስ ወንድ 22 ሴት 1 በድምሩ 23 ሠራተኞች ሲ/ሰ/ኮሌጅ እንዲሰለጥኑ ወረዳዎችን ባማከለና የምልመላን ደንብና መመሪያን በተከተለ መልኩ ተመልምለው ለክልል አቅ/ግን/ቢሮ ተላልፏል፡፡

9/ ከክልል ተዘጋጅተው የሚተላለፉ የአዳዲስ አሠራር መመሪያዎችና ደንቦች በሰው ሃብት ሥራ አመራር በኩል ወደ ተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶችና የሥራ ሂደቶች በተቀላጠፈ መልኩ እንዲተላለፉ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

- ከመ/ቤቱ ሥራ አገልግሎት የሚለቁ ሠራተኞችን በሚመለከት 2 ሠራተኞች በመ/ቤቱ ውስጥ ተመጣጣኝ መደብ ባለመኖሩ ምክንያት ወደ ዱራሜ ከተማ አስ/ርና ቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ ተመድበው ከነበጀታቸው የተሸኙ ሲሆን አንድ ሠራተኛ በት/ት ማነስ ምክንያት መንግስት ባስቀመጠው የመፍትሄ አማራጮች አቅጣጫ እድሜው 52 በላይ በመሆኑ በጡረታ እንዲገለል ተደርጓል፡፡
- በጽህፈትና ቢሮ አስተዳደር አገልግሎት መደብ ላይ የአንድ ሴክሬታሪ ታይፒስት ቅጥር ተፈጽሟል፡፡ ከአራት ወረዳዎች ማለትም ከዶዮገና ፣ከዳምቦያ፣ ከቀዲዳ ጋሜላና ከቃጫ ቢራ ወረዳ አቅ/ግን/ጽ/ቤቶች የ6 ሠራተኞች ቅጥር የተፈጸመበትን ማስረጃ ወደ ክልል ቢሮ ደርሶ ሥምምነት መጥቶላቸው በእያንዳንዱ ሠራተኛ እጅ ገብቷል፡፡
- በበጀት ዓመቱ ውስጥ በተለያዩ የአቅም ግንባታ ኘሮግራሞች አፈፃፀም የተሻለ ውጤት ላስመዘገቡ የወረዳ አቅ/ግን/ጽ/ቤቶች የማትጊያ ሽልማት ለመስጠት 2 ኮምፒውተሮች ተገዝተዋል፡፡

10/ በአቅም ግንባታ ኘሮግራሞች ላይ ለን/ሰቡና ለተጠቃሚዎች ወቅታዊ መረጃዎች ተሰብስበውና ተጠናቅረው እንዲሠራጩ ከማድረግ አንፃር ልዩ ልዩ ወቅታዊ መረጃዎች ከዞን ሴክተር መ/ቤቶች፣ ከወረዳዎች ፣ከዱራሜ ከተማ አስ/ር ፣ ከዱራሜ

ሆስፒታልና ከኢንደስትሪያል ኮሌጅ ተሰብስበው በማጥራትና በመተንተን ላይ ይገኛሉ፡፡ ከዞኑ አቅም ግንባታ ጽ/ቤቶችና ከሌሎችም ሴክተሮች የተሰበሰቡት መረጃዎች ለክልል አቅም ግንባታና ለሚመለከታቸው ክፍሎች እንዲተላለፉ ተደርጓል፡፡

- ተሰብስበው በዶክመንትነት የተያዙት መረጃዎች ወደ ኮምፒውተር የማስገባት ሥራም በአሁኑ ወቅት እየተከናወነ ይገኛል፡፡

11/ ሁሉም የዞን ፣የወረዳና የከተማ አስ/ር አቅ/ግን/ጽ/ቤቶች ያለፈውን የ5 ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ በመገምገምና የቀሪ ዓመታትን /2001-2002 / ዕቅድ በመከለስ እንዲሁም የ2001 ዓ/ም የ2ኛ መንፈቅ ዓመት እቅድ ከአዲሱ መሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጥ ትግበራ ጋር በማጣጣም ከልሰው ወደ ትግበራ በመግባት የዓመቱን እቅድ አከናውነዋል፡፡

- በበጀት ኮድና በየሥራ ሂደቱ /የወጪ ማዕከሉ/ በዝርዝር የቀረበው የቀጣይ 2002 በጀት ዓመት እቅድና በጀት በሴክተር ደረጃ ከተዘጋጀ በኂላ በሚመለከታቸው የሥራ ሂደቶችና የመምሪያው ኃላፊ ተተችቶና ተሻሽሎ ለሚመለከታቸው ክፍሎች እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡
- ከተለያዩ የሥራ ሂደቶች በቀረበውና በተቀመጠው የአፈፃፀም ስታንዳርድ መሠረት በሴክተር ደረጃ የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቷል፡፡
- በዞኑ ካሉት ወረዳዎች በግማሽ ያህሉ ማለትም በዳምቦያ፣ በአንጋጫ፣ በዶዮገና ወረዳና በዱራሜ ከተማ አስ/ር አቅ/ግን/ጽ/ቤቶች የል/ዕ/ዝ/ክ/ግ/ግ/መልስ ኦፊሰሮች መደብ ላይ ባለሙያ ያልተመደበበትና ክፍት በመሆናቸው ምክንያት በሥራ ሂደቱ በኩል የሚሠሩ ሥራዎች የሚፈለገውን ያህል አልተከናወነም፣ ከዞኑ አቅ/ግን/መምሪያ የዘርፉ ባለሙያ ከ19-24/10/2001 ዓ/ም በቼክ ሊስት ባደረገው ድጋፋዊ ክትትል ክፍት መደቦቹ በየወረዳው በሰኔ ወር በጀት በቅጥር እንዲሚሸፈኑ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- የዱራሜ ከተማ አስ/ር ማ/ዊ አገ/ት አቅ/ግን/ጽ/ቤትም የተፈጠረውን ክፍተት በባለሙያ ቅጥርም ሆነ የሥራ ሂደቱን እቅድ በማዘጋጀትና በሴክቶሪያል እቅድ በማካተት በኩል የራሱን ጥረት እንዲያደርግ ድጋፋዊ ክትትል ወቅት ከስምምነት ተደርሷል፡፡
- ከላይ የተጠቀሱትን የየወቅቱን ሪፖርቶችና እቅድ በወቅቱ በመላክ በቀደምትነትና በመልካም ተምሣሌትነት የሚጠቀሱት በ3ኛው ሩብ ዓመት ወቅት 1ኛ/ ዶዮገና 2ኛ / ጠምባሮ 3ኛ/ ሃደሮና ጡንጦ ዙሪያ ወረዳዎች ሲሆኑ በ4 ሩብ ማጠቃለያ ሪፖርትና የ2002 ዓም እቅድ በማቅረብ 1ኛ/ አንጋጫ 2ኛ / ዱራሜ ከተማ አስ/ር 3ኛ/ ቀ/ጋ/ወ/አቅ/ግ/ጽ/ቤቶች ናቸው፡፡

3.3. ያልተከናወኑ ዝርዝር ቁልፍ ተግባራት

- ለቪዲዮ ኮንፍራንስ የታቀደው አልተፈጸመም፣ምክንያቱም አስፈላጊ ማቴሪያሎች ባለመሟላታቸው ነው።
- የተሰበሰቡ መረጃዎች የማጥራትና በኮምፒውተር የማስገባት ሥራ አልተጠናቀቀም፣

## 4. በአባይት የትኩረት መስኮች

### 4.1 የታቀዱ ዝርዝር አባይት ተግባራት /ውጤቶች/

- በዞንና በወረዳ ደረጃ በመደበኛነት የቀጠሉ የሪፎርም ውይይቶችና ተግባራዊ የተደረጉባቸው መ/ቤቶች
- ለአገ/ት አሰጣጥ ቀልጣፋነት ምቹ የሥራ አካባቢ የፈጠሩ የዞንና የወረዳ ም/ቤቶችና የተደረገላቸው ድጋፋዊ ክትትል ፣
- በየደረጃው የተቋቋሙ የፈጣን ልማትና የመልካም  አስተዳደር ትግበራ ፎረሞች / ወጣቶች ሴቶች/
- በወቅቱ የተላለፉ ሪፖርቶችና የተጠናቀሩ መረጃዎች
- የባለሙያ ምልከታ ጉብኝት ተደርጎ በ2 ዙር የተሰጠ ድጋፋዊ ክትትልና ግብረ መልስ
  - ❖ የሰለጠነ የሰው ሀብት አጠቃቀምና የቪዲዮ ኮንፍረንስ ሥልጠናዎች የተደረገ ድጋፍና የአፈጻጸም ክትትል ግምገማና ሪፖርት
  - በዘመኑ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተመረቁ ምሩቃንን ከመ/ቤቶች የሰው ሀብት አጠቃቀም ፍላጎት ጋር በማጣጣም በፍትሃዊነት ለመመደብ የተደረገ ቅድመ ዝግጅት
  - በ61 የዞንና የወረዳ መ/ቤቶች ከሥልጠና በኂላ የተደረገ ድጋፋዊ ክትትልና ሪፖርት
  - በልማት ዕቅድ ዝ/ክ/ግ/ግ መልስ የሥራ ሂደት የተደረገ የአፈጻጸም ክትትል፣ግምገማና ግብረ መልስ ሥርዓት
  - በየሩብ ዓመቱ ተሰብስበው የጠናቀሩ ሪፖርቶችና ግብረ መልስ አሰጣጥ ሂደት
  - ❖ በኢኮቴ የሥራ ሂደት  በዞንና በወረዳ ሴ/መ/ቤቶች በቼክ ሊስት የተደረገ ድጋፋዊ ክትትል፣ ግምገማ፣ ግብረ መልስና ሪፖርት
  - ❖ በሰው ሀብት ሥራ አመራር ክትትል የተመዘነና የተደራጀ የሠራተኛ ውጤት ተኮር ዕቅድ አፈጻጸም መረጃ
  - ተደራጅተው የተቀመጡ ደንቦች፣መመሪያዎች፣አዋጆች እና በተዋረድ ለወረዳዎች የተላለፉ መረጃዎች
  - ❖ በመረጃ መሰብሰብና ማሰራጨት የሥራ ሂደት የተፈጸመ የአፈጻጸም ክትትል ግምገማና ግብረ መልስ ሂደት
  - ❖ በሥርዓተ ፆታና ኤች አይ ቪ/ኤድስ ሜይንስትሪሚንግ የተፈጠረ ግንዛቤ የኤች አይ ቪ/ኤድስን ሥርጭት ለመግታትና ለማጠናከር የተደረገ የበጀት ድጋፍ

- በመንግሥት መ/ቤቶች የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ የተዘረጋውን የአሠራር ሥርዓት ለማጠናከር የተሠራ ሥራ

### 4.2. የተከናወኑ ዝርዝር አባይት ተግባራት

❖ የሪፎርም ውይይትን በዞንና በወረዳ በሁሉም መ/ቤቶች ከመቀጠል አንፃር ፣

➢ ወደ አዲሱ የአሠራር ሥርዓት ለውጥ ትግበራ በገቡ በ7 የዞን መ/ቤቶችና በሃምሣ ሂደቶቻቸው በየሂደቱ የአገልግሎት አሰጣጣቸውን የእቅድ አፈፃፀማቸውንና የመረጃ አያያዛቸውን በእለታዊ ቃለ ጉባዔ መዝገብ እያሰፈሩ ጠንካራና ደካማ ጐኖችን እየገመገሙ የመወያየት ሁኔታ መቀጠሉን በ3 ዙር ድጋፋዊ ክትትል ወቅት የተሰበሰቡ መረጃዎችና ምልከታዎች አስገንዝበዋል፡፡

➢ ወደ አዲሱ የትግበራ ሂደት ባልገቡ 9 የዞንና በ72 የወረዳ መ/ቤቶች ቀደም ሲል በመደበኛነት በቡድን በየሣምንቱ የመወያየትና የመገማገም ሥልት መኖሩን ከምልከታና ከመ/ቤቶች ሪፖርት ሊጤን ተችሏል፡፡

❖ ለአገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋነት ምቹ የሥራ አካባቢ የፈጠሩ የዞንና የወረዳ መ/ቤቶችና የተደረገላቸው ድጋፋዊ ክትትል፣

➢ በትግበራ ሂደት ለገቡ የዞንና የወረዳ መ/ቤቶች አገልግሎት አሰጣጥን ቀልጣፋ ለማድረግ እያንዳንዱ የሥራ ሂደት እቅድ አዘገጃጀትን ከእቅድ አፈፃፀም ጋር ለማጣጣም በተጠናው ስታንዳርድ በሰዓት፣ በጊዜ፣ በጥረት /በተደራሽ ግቦች/ በመለየት መረጃዎችን በማሰባሰብና እርካታ በመመዘን በማኑዋሉ የተቀመጡ የሴክተሩን ልዩ ልዩ ቅጾች በመጠቀም ላይ መሆናቸውን የምልከታ መረጃ ያሣያል፡፡ ለአብነት ከሚጠቀሱት ሂደቶችም በንግድ ኢንዱስትሪ የትራንስፖርት ፣የሆቴሎች ፓርኮችና ቱሪዝም በፋይናንስ የክፍያ ግዥና ንብረት አስተዳደር በከተማ ልማት መምሪያና በፖሊስ መ/ቤቶች ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

➢ ጥናታቸው በመጠናቀቅ ላይ ባሉት በ81 መ/ቤቶች ለተገልጋይ ቅን፣ ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ ሥርዓት ዘርግቶ ከመሥራት አኳያ የመ/ቤቱን አድራሻ፣ የቢሮና የሠራተኛ አድራሻና ስለሚሰጧቸው አገልግሎቶች የአስተያየት መስጫ መዝገብና ሣጥን እንዲሁም ቅሬታ ሰሚ በመመደብ ተግባራዊ እያደረጉ መሆናቸው ታይቷል፡፡

❖ በ119 የገጠር ቀበሌያት በመልካም አስተዳደርና ፈጣን ልማት የተካሄደ ሕዝባዊ ውይይት፣

➢ በቃጫ ቢራ ወረዳ ለ588 አመራርና ሥራ አስኪያጆች ስለ መሬት መጠቀሚያ ግብር መመሪያ የአንድ ቀን ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ ይህም ወደየቀበሌ ወርዶ ሁሉም ግብር ከፋይ እንዲያውቀው ተደርጓል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ስለ ሞዴል አመራረጥ ስለ

ቀበሌ ኢንስፔክሽን አባላት አመራረጥ፣ ኃላፊነትና ተግባራት ግንዛቤ መፈጠሩን በወረዳው ከተደረገ ምልከታ ሊረጋገጥ ተችሏል፡፡

- በቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ ለ17ቱም የቀበሌ አመራሮች ሥራ አስኪያጆች፣ የኢንስፔክሽን አባላትና ከቀበሌያት ለተውጣጡ የእድር መሪዎች በድምሩ ለ207 ተሣታፊዎች ስለ እርዳታ እህል አከፋፈልና አጠቃቀም ስለ ኢንስፔክሽን ተግባራትና ስለ ሞዴሎች አመራረጥ የአንድ ቀን ውይይት መደረጉን ከወረዳው በተደረገው የድጋፋዊ ክትትል መረጃ ሊገኝ ተችሏል፡፡
- በአንጋጫ ወረዳ የመልካም አሰተዳደር ፓኬጅ አዋጅን ለመተግበር 185 የቀበሌ አመራር ሥራ አስኪያጆችና የኢንስፔክሽን ቡድን አባላት የአንድ ቀን ውይይት ተካሂዷል፡፡
- በዳምቦያ ወረዳ የፓኬጁን አፈፃፀም ለመተግበር ለ136 የቀበሌ አመራር ለ17 የኃይማኖት መሪዎችና ለ17 ታዋቂ ግለሰቦች በድምሩ ለ187 ተሣታፊዎች የአንድ ቀን ግንዛቤ መፍጠሪያና ውይይት መካሄዱን የምልከታው መረጃ አመላክቷል፡፡

❖ *ወቅታቸውን ጠብቀው የተዘጋጁ መረጃዎችና ሪፖርቶች ፣*

- መረጃዎችን በሚመለከት በተለያዩ ጊዜያት ከዞንና ወረዳ ትግበራ በገቡ መ/ቤቶችና ሂደቶች፣
  - ሥልጠና የወሰዱትን አኃዝ
  - ያልወሰዱትን አኃዝ
  - በዋና የሥራ ሂደት የተመደቡትንና የመደቦችን ብዛት
  - በደጋፊ የሥራ ሂደት የተመደቡትንና የመደቦችን ብዛት
  - ምደባ ያልተካሄደባቸውን የመደቦች ፣የሥራ ሂደቶችና የሠራተኞችን አኃዝ በተከታታይ ለ3 ዙር በዞንና በወረዳ በተዘጋጁ ቅጾች እየተሞላ ለሚመለከተው አካል እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡
- ለአንድ ዙር ትግበራ ያልገቡትን የዞን መ/ቤቶች የሠራተኛ ብዛት የዴስኮችን የቡድኖችን ብዛት የሚገልጽ መረጃ ተሰብስቦ ተላልፏል፣
- ሪፖርትን በሚመለከት፣
  - የለውጥ ኘሮግራሞች ኘሮጀክት ዋና የሥራ ሂደት በ2 ዙር የ2 ሩብ ዓመት ሪፖርት ከየወረዳዎች/ከ8ቱም/ በማሰባሰብ የሂደቱን ሪፖርት ለሚመለከተው አስተላልፏል፣
  - የ2ኛ 6 ወራት የግማሽ ዓመት ሪፖርት በታቀዱ በተከናወኑና ባልተከናወኑ ውጤቶች ተለይተው በሪፖርት ፎርማት መሠረት ለሚመለከተው /ኃላፊና የሥራ ሂደት/ እንዲላክ ተደርጓል፡፡

❖ በ2000 ዓ/ም ከከፍተኛ የት/ት ተቋማት በዲግሪ መርሃ ግብር ት/ታቸውን ጨርሰውና ተመርቀው ከተመዘገቡት 108 ምሩቃን መካከል 68 በዞንና በወረዳዎች በሚገኙ ክፍት

የሥራ መደቦች ተወዳድረው ሲቀጠሩ የተቀሩት 24 ተመራቂዎች በፌዴራል ፖሊስ፣ ከአ/አ ቂርቆስ ክ/ከተማና በሌሎችም ቦታዎች ሲቀጠሩ 16 ያህሎቹ በክልል ደረጃ መቀጠር እንዲችሉ ለሚመለከተው አካል የማስተላለፍ ሥራ ተሠርቷል፡፡

❖ የ2001 ዓ/ም የከፍተኛ ት/ት ምሩቃን መረጃ በመሰብሰብ ላይ ያለ ቢሆንም የምረቃው ኘሮግራምም ሆነ የአመልካቾቹ ምዝገባ ገና ስለሆነ አልተጠናቀቀም፡፡

❖ የቪዲዮ ኮንፍራንሲንግ ሥልጠና በሚመለከት በአሁኑ ወቅት በአገር አቀፍ ደረጃ እየተካሄደ ያለው የግብርናና ገጠር ኢኮኖሚ ልማት በቪዲዮ ኮንፍራንሲንግ በዞናችንም ደረጃ በ3 ማዕከላት እየተሰጠ ሲሆን ይህንኑ የዞኑ አቅ/ግንባታ መምሪያ የማስልጠንና የማስተባበር ተግባር እየፈጸመ ይገኛል፡፡

❖ በሰው ኃብት ሥራ አመራር በኩል የሴክተሩን ሠራተኞች እቅድ አፈፃፀም እየተመዘነና እየተደራጀ ይገኛል፡፡

❖ በአዲሱ የአሠራር ትግበራ ላይ ከክልል የሚተላለፉ መመሪያዎችና ደንቦች በአግባቡ እየተደራጁና ለሚመለከተው እንዲተላለፉ በመደረግ ላይ ናቸው፣

❖ በሴክተሩ በሚገኙ በሁሉም የሥራ ሂደቶች በኩል የተጀመሩትን የአሠራር ሂደት ለውጥ ፣ የሪፎርምና የመልካም አስ/ር ድጋፋዊ ክትትልና ግብረ መልስ አሰጣጥ ሥራዎች በ4ኛ ሩብ ዓመት ተጠናክረው በመሠራታቸው የተሻለ ርብርብ በመደረጉ የታለሙ ግቦች በተሣካ ሁኔታ ተፈጽመዋል፡፡

### *4.3. ያልተከናወኑ አባይት ተግባራት /ውጤቶች /*

በአባይት የታቀዱ ተግባራት ከ1-4 የተጠቀሱት ሁሉም በ100% ተከናውነዋል፡፡ /ያልተከናወኑ የሉም/

5. የእቅድ አፈፃፀም ደረጃ በመቶኛ

5.1. በቁልፍ ውጤቶች 98%

5.2. በአባይት ውጤቶች 99.5%

5.3. በእቅድ አፈፃፀም ወቅት የነበሩ ጠንካራና ደካማ ጐኖች

6.1 ጠንካራ ጐኖች

B.P.R ትግበራ ቀጣይነት እንዲኖረው አመራሩ በተለያዩ ጊዜያት ሥልጠና በመቀበል ወደ ባለቤትነት ተሸጋግሮ ማስቀጠሉና ግንዛቤ እንዲፈጠር በየእርከኑ የተለያዩ መድረኮችን መፍጠር መቻሉ

- ከተገልጋይ ለሚቀርቡ አቤቱታዎችና ቅሬታዎች ፈጣን ምላሽ ከመስጠት አኳያ ችግሮቹ ከተፈጠሩበት መ/ቤት ጋር በመነጋገር በማቃለል ጊዜ ወጪና ጉልበት ከብክነት መዳኑ

- ወደ ትግበራ የገቡ ሠራተኞች ባጭር ጊዜ ከሥልጠና መነሻ ውጤታማ ሥራ መሥራት መቻላቸው
- ከሴክተሮች ጋር ጤናማ ግንኙነት በመፍጠር ፈጣን የመረጃና የሪፖርት ሥራዎች መሠራታቸው
- የቁሳቁስና የተሽካሪካሪ ዕጥረት ቢኖርም ባለው አቅም አሟጦ ለመጠቀም መቻሉ

6.2 ደካማ ጐኖች

- ወደ ትግበራ ባልገቡ መ/ቤቶች የነበረው የሪፎርም ውይይት በሠራተኛው ዘንድ በመደበኛነት ተጠናክሮ በሪፖርት ያለመደገፍ
- ወደ B.P.R ትግበራ በገቡ የወረዳዎች ሂደቶችና ከቀሪዎችም ላይ በቼክ ሊስት የተደገፈ የዕቅድ አፈጻጸም ድጋፋዊ ክትትልና መረጃ እንደአስፈላጊነቱ ያለመያዝ
- ከወረዳ አቅም ግንባታ ጽ/ቤቶች ወቅታዊ ሪፖርትና በ B.P.R ምደባ ስለተያዙና ስላልተያዙ የሥራ ሂደቶች አፋጣኝ ምላሽ ባለመሰጠቱ / መንጠበጠብና መዘግየት/
- የተከለሰን ዕቅድ በተሟላ መልኩ ከወረዳ ሂደቶች ጋር በቲም ቻርተር አለማጽደቅ

7. **በዕቅድ አፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች**

- የ B.P.R ትግበራን ለማፋጠን በተጀመረባቸው የሥራ ሂደቶች የተመቻቸ የሥራ አካባቢን ለመፍጠር ከበጀት ጋር የተያያዙ ያልተፈጸሙ ግዢዎች
- B.P.R ትግበራ በገቡ የሥራ ሂደቶች የተያያዘ የተገናኘና ባንድ አከባቢ የተሰጠ ቢሮ አለመኖር
- ወደ ትግበራ በገቡ የሥራ ሂደቶች ለባለሙያዎች የተጠናከረ የኮምፒዩተር ሥልጠና አለመስጠትና የኮምፒዩተሮችና አላቂ ዕቃዎች አለመሟላት
- ጥናታቸው ባልተጠናቀቀባቸው መ/ቤቶች ያለውን የዕቅድ አፈጻጸም ለመከታተልና በደጋፊ የሥራ ሂደት የተመደቡ ሠራተኞች በበቂ ግንዛቤ ዕቅዳቸው አዘጋጅተው አለመንቀሳቀስና ባንዳንድ መ/ቤቶች የደጋፊ ሥራ ሂደት ሠራተኛ ያለመመደብ
- የፋይናንስ አሠራርና የመ/ቤቶች ዕቅድ ክንውን ተጣጥሞ ያለመሄድ

8. **የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች**

- ከበጀት ጋር ባለው ችግር ባለው ቁሳቁስና የጽህፈት መሣሪያ በመገልገል አገልግሎት መስጠት መቻሉ
- ባንዳንድ መ/ቤቶች የ B.P.R የተጠኑ የሥራ ሂደቶችን ወደ አንድ የሕንፃ ክፍሎች አያይዞ ለመሥራት መጀመሩ
- የIT ሥልጠና ዕጥረት ቢኖርም በነባር ባለሙያዎችና በወረዳ የኢኮቴ ማዕከል ባለሙያዎች በመታገዝ ሥራ መሠራቱ
- በደጋፊ የሥራ ሂደቶች ላይ የግንዛቤ ክፍተት ባለባቸው የአሠራር አቅጣጫና የማኑዋሎች ሥርጭት መካሄዱና መሠራቱ
- በደጋፊ የሥራ ሂደቶች በየመ/ቤቶች የሠራተኛ ክፍተት ባሉባቸው መደቦች በየወረዳውና በዞን ሴክተሮች ከተሰበሰበው መረጃ በመነሳት የሰው ኃይል እንዲሟላ ለአማራጭ መፍትሔ አስተግባሪ በማቅረብ ምደባ እንዲከናወን መደረጉ

- የሪፖርትንና የመረጃን ክፍተት ለመሙላት በተደጋጋሚ የስልክ መልዕክቶችን በማስተላለፍ እና በመቀበል መሠራት መቻሉና ወዘተ.. ናቸው፡፡

## 9. ለወደፊት ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

- የተጀመረው የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራ (B.P.R) በዞናችን ባሉት በሁሉም ሴክተሮች ወደ ሙሉ ትግበራ እንዲሸጋገርና አዲሱ አሠራር የአመራሩና የሠራተኛው ባህል ሆኖ እንዲቀጥል በየደረጃው ያለው አመራር የባለቤትነትና የቁርጠኝነት መንፈስ ተላብሶ መቀጠል ያለበት ጉዳይ መሆኑን በየደረጃው ያሉ አመራሮችና ኃላፊዎች ቁልፍ አጀንዳቸው መሆኑን አውቀው መቀጠል እንዳለባቸው
- ወደ ትግበራ በተሸጋገሩ መ/ቤቶች ክፍት የሥራ ሂደት መደቦች በምደባም ሆነ በቅጥር ቅድሚያ ተሰጥቶባቸው ሊሟሉ እንደሚገባ
- የICT ሥልጠናና ቁሳቁሶች በተለያየ ሁኔታ ከመንግሥትም ከረጂ ወገንም እንዲሟሉ መረባረብ ወዘተ.. ናቸው፡፡
- ከሚከናወኑ ቀሪ ተግባራት ጋር በዞንና በወረዳ ደረጃ የአጫጭር ሥልጠናዎችንና የዕቅድ አፈጻጸም ድጋፋዊ ክትትሎችን በባለሙያ በመታገዝ መደገፍና ግብረ-መልስ መስጠት
- የሪፎርም መደበኛ ውይይትን አጠናክሮ መቀጠልና የአመራሩ ሚና የጐላ ድርሻ እንዳለው ማስገንዘብ
- የተሻለ አፈጻጸም ካላቸው መ/ቤቶች በዞንና በወረዳ ደረጃ የልምድ ልውውጥ ኘሮግራም በማዘጋጀት ተሞክሯቸውን ማስፋፋት
- እስከአሁን ላልተፈጸሙ ውጤቶች ብርቱ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ

## 10. ማጠቃለያ

በአጠቃላይ የመንግሥት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በተሻለ ፍጥነትና ጥራት እንዲፈጸሙና በየመ/ቤቱ የሚጠበቁ ለውጦች እውን እንዲሆኑ የአቅም ግንባታ መምሪያ ሪፎርሙን ከማስቀጠል አንጻር የተጣለበት ኃላፊነት እጅግ ከባድ መሆኑ ይታመናል፡፡ ስለዚህ ቀጣዩ የ2002 ዓመት በጥቅሉ የዕቅድ አፈጻጸማችንና አጠቃላይ ዓመታዊ ግቦቻችንን የሚያሣኩ ተግባራት ሙሉ በሙሉ ተከናውነው የታለሙ ውጤቶችም ተጨብጠውና የግብ ስኬቶቻችን ተረጋግጠው የሚታዩበት ስለሆነ በዋናነት የቢፒአር ትግበራና የሠራተኛ ውጤት ተኮር ዕቅድ ዝግጅት እስከምዘና በማካተት የተጀመሩትን የሪፎርምና የመልካም አስተዳደር ድጋፋዊ ክትትል ሥራዎችን አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል፡፡